# ኢየሱስ ማነው?

በፊልጶስ ቂሣርያ በመዋዕለ ሥጋዌው ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን አንድ ዓይነት ጥያቄ ጠይቋቸው ነበር። ጥያቄውም ዓለም ማን እንደሚለው ነበር። ሲናገሩ መልሱ የተለያየ ነበር፤ አንዳንዶቹ ኤልያስ ነው ሌሎቹ ደግሞ ኤርምያስ ነው ሌሎቹ ደግሞ ከነቢያት አንዱ ነው ይሉ እንደነበረ መለሱለት። ኢየሱስም ዓለም እንዳላወቀው ስለሚያውቅ እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ? በማለት ጥያቄውን ወደደቀመዛሙርቱ ለወጠው። ከደቀመዛሙርቱም መካከል አንዱ "አንተ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" ብሎ በመመለሱ "ብፁዕ ነህ" ብሎ ጌታ እንደመለሰለት ተመዝግቧል።

"ኢየሱስም ወደፊልጶስ ቂሣርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ እነርሱም አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ ሌሎችም ኤልያስ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት እርሱም እናንተስ እኔን ማን እንደሆንሁ ትላላችሁ አላቸው፤ ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡- አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ..." አለው ይላል የእግዚአብሔር ቃል (ማቴ16፥14-17)።

ዛሬም በዘመናችን ያን ጊዜ ዓለም የኢየሱስን ማንነት እንዳላወቀች ሁሉ ማንነቱን አታውቅምና በጉያዋ ያቀፈቻቸው ኤርምያስ፣ ኤልያስ፣ መጥምቁ ዮሐንስ ባዮች ነቢይ ባዮች እንዳያሳስቱን ማንነቱን ልናውቅ ልናሳውቅ ለሚጠይቁን ሁሉ ልንመልስ ይገባልና።



www.ethiopianorthodox.org

የኢየሱስን ማንነት አውቀው ለሚመልሱ ሕያው ጸጋ ይሰጣቸዋል የተወሠኑትን ብንጠቅስ

- ብፁዓን ይሰኛሉ (ማቴ 16፥17)
- ዓለምን ድል የሚነሱበት ኃይል ይሠጣቸዋል (1ዮሐ 5፥5-7)
- የዘለዓለም ሕይወት ይሰጣቸዋል (1ዮሐ 5፥11 ዮሐ 20፥30-31)

እነዚህንና ሌሎችንም የእግዚአብሔር ጸጋዎች ለመቀበል እንድንችል ማንነቱን በጥንቃቄ እናጥና።

ይህን ጥያቄ መመለስ እንችል ዘንድ ስለማንነቱ የሚመሰክሩ ምስክሮችን እንመልከት ምድራዊው ፍጥረት ከሰማይ ካልተሰጠው በቀር እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ ትክክለኛውን መልስ መመለስ አይችልምና።

## ስምንቱ የኢየሱስ ማንነት ምሥክሮች

### 1. እግዚአብሔር አብ፤

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አብ ስለኢየሱስ የሚመሠክር ማንነቱን የሚያውቀው ተቀዳሚ ምሥክር መሆኑ ተገልጿል። አዎን የባሕርይ ዕውቅና የሚያውቀው የባሕርይ አባቱ ነውና አጥጋቢ ምሥክር ነው። (ማቴ 11፥27)

ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ሆይ አርዮስ ኢየሱስን ማን እንዳለው፣ ንስጥሮስ ማን እንዳለው፣ ጳውሎስ ሳምሳጢ ማን እንዳለው፣ መሐመዳውያንም ማን እንዳሉት ከታሪክ አንብበህ በጆሮህም ሰምተህ ይሆናል። የአንሲ ጂሰሶችንም (ኢየሱስ ብቻ ባዮችንም) ኢየሱስ ማንነት ሰምተህ ይሆናል።

ነገር ግን አብ የሚመሠክርለት በቅዱስ መጽሐፍ የተገለጸው ኢየሱስ በእርግጥ እነሱ እንደሚሉት መስሎህ ይሆን? አይደለም። የእኛው



www.ethiopianorthodox.org

ኢየሱስ እንደ አርዮስ ባሕል ያልተፈጠረ እንደንስጥሮስ ባህል ያልተካፈለ፣ እንደ ጳውሎስ ሳምሳጢ ባህል ከጊዜ በኋላ ያልተገኘ፣ እንደ አውጣኪ ባህል ያልተለወጠ እንደ መሐመድ ሃሣብ ተራ ነቢይ ያይደለ አብም መንፈስ ቅዱስም የማይባል ሕያው ጌታ መሆኑን ልብ ብለህ ተመልከት። ለመሆኑ ከላይ የተጠቀሱት መናፍቃንና ሌሎችም መናፍቃን ስለኢየሱስ የሚናገሩት ከስምንቱ ቀዋሚ ምሥክሮች ጋር አብሮ ይሄድ ይሆንን? እስኪ በእግዚአብሔር ቃል እንፈትነው።

### የአብ ምሥክርነት

"አብ እንደላከኝ ስለእኔ ይመሠክራልና የላከኝ አብም እርሱ ስለእኔ መሥክሮአል።" ዮሐ 5፥37 ይላል የእኛ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ። የት ላይ መሠከረ የሚል ጠያቂ ቢኖር፦

#### 1.1 በዮርዳኖስ፤

". . . በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" አለ። (ማቴ 3፥17) "የምወድህ ልጄ አንተ ነህ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅ ከሰማያት መጣ" (ማር 1፥11) ተብሎ ተጽፏልና በጊዜ ጥምቀት በባሕረ ዮርዳኖስ ነዋ ብለን እንመልስለታለን።

#### 1.2 በደብረ ታቦር፤

". . . እነሆም ብሩህ ደመና ጋረዳቸው እነሆም ከደመናው በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።" (ማቴ 17፥5-6) ተብሎ በወንጌለ መንግሥቱ ስለተጻፈ በደብረታቦርም መስክሮለታል።

### 1.3 በፊልጶስ ቂሣርያ በልሳነ ጴጥሮስ፤

"የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ" (ማቴ 16፥17) ብሏልና መድኃኒታችን። በልሳነ ጴጥሮስም አብ መስክሮለታል።

ሐዋርያው ዮሐንስም ይህን የአብን ምሥክርነት መቀበል እንዳለብን የሚከተለውን ጽፏል።

"የሰውን ምሥክር ብንቀበል የእግዚአብሔር ምሥክር ከእርሱ ይልቅ ይበልጣል ስለልጁ የመሠከረው የእግዚአብሔር ምሥክር ይህ ነውና። በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምሥክር አለው። በእግዚአብሔር የማያምን እግዚአብሔር ስለልጁ የመሠከረውን ምሥክር ስላላመነ ሐሰተኛ አድርጎታል።" (1ዮሐ 5፥9-11)

ከዚህ ላይ በመጠኑ የጠቀስናቸው ጥቅሶች አብ ስለልጁ ምን ያህል እንደመሠከረ ግልጽ የሚያደርጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ናቸው። እንግዲህ ከሰው ምሥክር የእግዚአብሔር ይበልጣልና አብ ስለባሕርይ ልጁ የሚያስተምረንን እናዳምጥ ሁላችንም ከእግዚአብሔር የተማርን እንሆን ዘንድ አሜን ብለን የባሕርይ አባቱ ስለልጁ የሚያሳውቀንን ለማወቅ ዓይነ ልቦናችንን እንግለጥ።

## 2. የመንፈስ ቅዱስ ምሥክርነት፤

ስለ ኢየሱስ ማንነት ከሚመሠክሩት ስምንት ምሥክሮች መካከል አንዱን (አብን) ከላይ ተመልክተናል። የባሕርይ አባቱ አብ ስለልጁ የመሠከረውን ከላይ እንደተመለከትን ከዚህ ደግሞ የባሕርይ ሕይወቱ መንፈስ ቅዱስ ስለአካላዊ ቃል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥክር እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ ተናግሯል። "...ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ



www.ethiopianorthodox.org

የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሠክራል።" (ዮሐ 15፥26-27) በማለት ነው ክርስቶስ ኢየሱስ የተናገረው።

## መንፈስ ቅዱስ እንዴት መሠከረለት

### 2.1 በዮርዳኖስ፤

"እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ።" ማቴ 3፥16, ማር 1፥10, ሉቃ.3፥22) በእጅ ጠቁሞ እንደማመልከት ነው።

### 2.2 በበዓለ ሃምሣ፤

ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ እንዲህ ብሎ ነበር "እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ እኔ እንድሄድ ይሻላችኋል፤ እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደእናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ። እርሱም መጥቶ ስለኃጢአት ስለጽድቅም ስለፍርድም ዓለምን ይወቅሣል ስለኃጢአት፣ በእኔ ስለማያምኑ ነው ስለጽድቅም ወደአብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው ስለፍርድም የዚህ ዓለም ገዥ ስለተፈረደበት ነው።" (ዮሐ 16፥7-11)

በዚህ ምንባብ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ልብ ብንል በኢየሱስ ክርስቶስ አለማመን ኃጢአት መሆኑን፣ ኢየሱስ ወደአብ ማረጉ ጽድቅ (እውነት) መሆኑን የዚህ ዓለም ገገር ዲያብሎስ በኢየሱስ የተፈረደበት መሆኑን ለመመሠከር እንደመጣ ነው የተናገረው። በዚሁ ክፍል ደግሞ "...የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል።" (ዮሐ 16፥13) በማለት የተናገረውን ልብ እንበል።

ክርስቲያኖች ሆይ "አማን አማን እብለክሙ እውነት እውነት እላችኋለሁ" ብሎ ያስተማረ ስለእውነት ሊመሠክር የመጣ (ዮሐ 18፥35) ራሱ እውነት የሆነ ማነው? ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለምን? (ዮሐ 1፥4-6) እንግዲያውስ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ሰዎችን መርቶ ያደረሰበት እውነት ኢየሱስ ነው። ይህንንም በበዓለ ሃምሣው ታሪክ እንገነዘበዋለን። የሐዋ 2፥1-8 ያለውን ክፍለ መጽሐፍ ስናነብ መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ከወረደ በኋላ በቅ/ጴጥሮስ ስብከት ሦስት ሺህ ነፍሳት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት በኢየሱስ በማመን ወደ እውነት እንደደረሱ እንገነዘባለን። በዚህ ታሪክ የምንገነዘበው መንፈስ ቅዱስ በሰዎች አድሮ እንዴት እንደመሠከረለት ነው።

## 2.3 ሰዎችን ሁሉ ለርሱ ጌትነት በማናገር ይመሠክርለታል፤

ሰዎችን ስለእውነት እንደሚያናግር የሚከተለውን እንመልከት "ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር ኢየሱስ የተረገመ ነው የሚል እንደሌለ በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በቀር፦ ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ።" (1ቆሮ 12፥3-4) ይላል የእግዚአብሔር ቃል።

ክርስቲያን ሆይ ስለ ኢየሱስ ክርሰቶስ የምታምነው እምነት በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት የተቀበልከው ስጦታ በመንፈስ ቅዱስ ያፈራኸው ፍሬ መሆኑን ተገነዘብክን? (ገላ. 5፥22)

## 3. መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ፤

ከስምንቱ ምሥክሮች ሁለቱን አብና መንፈስ ቅዱስን ከተመለከትን ወደ ሦስተኛው ምሥክር እንሂድ፤ ሦስተኛው ምሥክር



www.ethiopianorthodox.org

መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ ነው። መጥምቁ ዮሐንስ ስለኢየሱስ ሊመሠክር ከእግዚአብሔር እንደተላከ የሚናገሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ቃል በቃል እንከታተል።

"ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበር ሁሉ በእርሱ (ኢየሱስ) በኩል እንዲያምኑ ይህ (ዮሐንስ) ስለብርሃን (ኢየሱስ) ይመሠክር ዘንድ ለምሥክር መጣ ስለብርሃን ሊመሠክር መጣ እንጂ እርሱ ብርሃን አልነበረም (ዮሐ1፥6-8) በዚህ ክፍለ - ቃለ - እግዚአብሔር ዮሐንስ በመምህርነት የመጣበትን ዓላማ ልብ ልንል ይገባል።

በዚህ ክፍል ሌላውን መረጃ እንመልከት ዮሐንስ ስለእርሱ (ኢየሱስ) መሠከረ እንዲህም ብሎ ጮኸ "ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ከእኔ በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል ስለእርሱ ያልሁት ይህ ነበር። (ዮሐ1፥15-16) በዚህ ክፍል ደግሞ ሌላውን መረጃ እንመልከት።

"አይሁድም አንተ ማን ነህ? ብለው ይጠይቁት ዘንድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት ጊዜ የዮሐንስ ምሥክርነት ይህ ነው መሠከረም አልካደምም.... የጌታን መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ እኔ ነኝ አለ።" (ዮሐ 1፥19-23)

"ዮሐንስ መልሶ እኔ በውኃ አጠምቃለሁ ዳሩ ግን እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል። እኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከብር ይህ ነው አላቸው።" (ዮሐ 1፤26-27)

"በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደእርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፦ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ... ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሠከረ መንፈስ ከሰማይ እንደርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ

... እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ መሥክሬአለሁ (ዮሐ 1፥29-36)።

"ዮሐንስ መለሰ እንዲህ ሲል ከሰማይ ካልተሰጠው ሰው አንዳች ሊቀበል አይችልም ... ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው። ቆሞ የሚሰማው ሚዜው (ዮሐንስ) ግን በሙሽራው (ኢየሱስ) ድምፅ እጅግ ደስ ይለዋል። እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ እርሱ (ኢየሱስ) ሊልቅ እኔ ላንስ ያስፈልጋል ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው። ከምድር የሚሆነው (ዮሐንስ) የምድር ነው። የምድሩንም ይናገራል ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው ያየውንና የሰማውንም ይህን ይመሠክራል ምሥክሩንም የሚቀበለው የለም ምሥክሩን የተቀበለ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደሆነ አተመ" (ዮሐ 3፥27-33)

ይህን ከዚህ በላይ ያነበብነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በማጽደቅ ኢየሱስ እንዲህ በማለት ተናገረ። "እናንተ ወደ ዮሐንስ ልካችኋል እርሱም ለእውነት (ኢየሱስ) መሥክሮአል እኔ ግን ከሰው ምሥክር አልቀበልም እናንተ እንድትድኑ ይህን እላለሁ እንጂ" (ዮሐ 5፥33-34) ሰዎች ሆይ ዮሐንስ ከእግዚአብሔር ተልኮ ስለልጁ የመሠከረውን ምሥክርነት ልብ እንበል እንቀበለው እንመነው።

## 4. *መለኮታዊ ሥራው፤*

የዓለም ቤዛ ወልደአብ ወልደማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር "... እኔ ግን ከዮሐንስ ምሥክር የሚበልጥ ሌላ ምሥክር አለኝ። አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ሥራ ይህ የማደርገው ሥራ አብ እንደላከኝ ስለእኔ ይመሠክራልና።" አለ (ዮሐ 5፥36) መፍቀሬ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ለመሆኑ ይፈጽመው የነበረው መለኮታዊ ሥራው ፍጹም ጌትነቱን፣ አምላክነቱን፣ መለኮታዊነቱን የሚገልጽ ነው።



### 4.1 *ትምህርቱ፤*

መለኮታዊነቱን የሚገልጽ ነበር፣ እርሱ በሚያስተምርበት ጊዜ የባሕርይ አምላክ እንደመሆኑ፣ ሠራኤ ሕግ፣ ሐጋጌ ሕግ እንደመሆኑ በሥልጣን እኔ እንዲህ እላችኋለሁ በማለት ያስተምር ነበር እንጂ እንደ ቀደምት ነቢያት "ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር" "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" በማለት አልነበረም "እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል. . . እኔ ግን እላችኋለሁ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርሷ ጋር አመንዝሯል . . . እኔ ግን እላችኋለሁ ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል . . . እኔ ግን እላችኋለሁ ክፉውን አትቃወሙ . . . እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ. . ." (ማቴ 5፥21-46) ይህን አምላካዊ ቃል የሰማው እግሩ ሥር የነበረው ሐዋርያው ቅ/ማቴዎስም እንዲህ ጽፏል። "ኢየሱስም ይህን ነገር በጨረሰ ጊዜ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ እንደጻፎቻቸው ሳይሆን እንደባለሥልጣን ያስተምራቸው ነበር።" (ማቴ 7፥28-29) በማለት፡ አሁን የተራራውን ስብከት የሰማ ክርስቲያን መቼም አምላካዊ ሥልጣን የሌለው ተራ ፍጡር በሥልጣን ያን ያህል ሠራኤ ሕግ ለመሆን እንደማይችል ይገነዘባል።

### 4.2 *ፈዋሽነቱ፤*

ኢየሱስ ክርስቶስ አጋንንትን ሲያወጣ ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ ወድቆ ተነሥቶ ሳይሆን በሥልጣን ውጣ በማለት ነበር አጋንንትን የሚያስወጣው እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ስለነበር በእግዚአብሔር ስም መቃወም፣ ስመ እግዚአብሔርን መጥራት አላስፈለገውም። ፍጡር እንጂ ስመ እግዚአብሔርን መጥራቱ ፍጡር በመሆኑ ኃይል ፈልጎ ነው? ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የኃይል ጌታ ነውና አጋንንትን ለማስወጣት

www.ethiopianorthodox.org

የሚከተለውን ብቻ ይናገር ነበር። "ዝም በል ከእርሱም ውጣ! ብሎ ገሰፀው፤ ጋኔኑም በመካከላቸው ጥሎት ወጣ።" (ሉቃ4፥35-36) በአጋንንት ላይ ሙሉ ሥልጣን ለሐዋርያት እና ለተከታዮቹ መስጠቱም የባሕርይ አምላክነቱን ይገልጻል (ማቴ 10፥1-10, ማር 16፥17) አጋንንትን እንዲያወጡ ለሐዋርያት ሥልጣን የሰጣቸው ሥልጣኑ የባህርዩ ቢሆን አይደለምን? የተሰጠውን ለሌላ እንዴት ሊቸረው ይችላል?

## 4.3 በሥርየተ ኃጢአት፤

ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአትን የሚያስተሠርየው ከደዌ የሚፈውሰው በሥልጣኑ ነበር እንጂ ከእርሱ የተለየ ሌላ አምላክ ኑሮበት የዚያን ስም ጠርቶ ወድቆ ተነሥቶ አልነበረም። ይህን በተመለከተ "አንተ ሰው ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው ጻፎችና ፈሪሳውያንም ይህ የሚሳደብ ማነው?" ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአትን ሊያስተሠርይ ማን ይችላል? አሉ" (ሉቃ 5፥20-21) ይላል የእግዚአብሔር ቃል።

አሁንም ክርስቲያኖች! አበው ቀሳውስት "ይፍቱኝ" ሲባሉ "እግዚአብሔር ይፍታህ" ይላሉ እንጂ ፈትቻችኋለሁ አይሉም ምክንያቱም በሥልጣኑ ይቅርም የሚል የሚፈርድም እግዚአብሔር ነውና ኢየሱስ ግን እግዚአብሔር በመሆኑ ኃጢአትን በሥልጣኑ ይቅር ይል ነበር ሥልጣኑም የጸጋ አለመሆኑን የሚያስገነዝብ ነገር ለቤተክርስቲያን የማሠርና የመፍታት ኃጢአትን ይቅር የማለት ሥልጣን ሰጥቷታል (ማቴ 18፥18 ዮሐ 20፥23) የባሕርይ ሥልጣኑ ባይሆን ለሌላ ሊቸረው ባልቻለም ነበር የተሰጠው ነውና። ከእግዚአብሔር የተሰጠን ሥጦታ ተሰጪ ለሌላ ሊሰጠው አይቻለውምና ተቀባይ ተሰጭ ስለሆነ ጸጋው ለሱ ተሰጠው እንጂ ለሌላው ሊሰጠው አልተቀበለውምና።



## 4.4 በሥነ ፍጥረት ላይ ያለው መለኮታዊ ሥልጣን፤

ማዕበል፣ ሞገድ፣ ውኃ፣ ነፋስ፣ ፍጥረታት በሙሉ ድምጹን በመስማት ይታዘዙለታል። "እርሱም ነቅቶ ነፋሱንና የውኃውን ማዕበል ገሰፃቸው ተወም ፀጥታም ሆነ . . . እርስ በእርሳቸው እንዲህ ነፋሳትንና ውሃን የሚያዝ ለእርሱም የሚታዘዙለት ይህ ማነው? አሉ" (ሉቃ 8፥24-25) አዎን ሥነ ፍጥረታት የሚታዘዙለት ሁሉን በቃልነቱ ከዊን የፈጠረ አካላዊ ቃል ወልደ አብ ወልደማርያም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እንጂ ሌላ አይደለም እርሱ ሁሉን ፈጥሯልና ሁሉ ለእርሱ ይታዘዛል። (ዮሐ 1፥3)

## 4.5 ሙታንን በሥልጣኑ ያስነሣል፤

"በነገውም ናይን ወደምትባል ወደ አንዲት ከተማ ሄዱ፤ ደቀመዛሙርቱም ብዙ ሕዝብም ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ። ወደ ከተማይቱም በር በቀረበ ጊዜ እነሆ የሞተ ሰው ተሸክመው አመጡ እርሱም ለእናቱ አንድ ልጅ ነበረ። እርስዋም መበለት ነበረች፤ ብዙም የከተማ ሕዝብ ከእርስዋ ጋር አብረው ነበሩ፤ ጌታም ባያት ጊዜ አዘነላትና፡- አታልቅሽ አላት ቀርቦም ቃሬዛውን ነካ የተሸከሙትም ቆሙ፤ አለውም አንተ ጎበዝ እልሃለሁ ተነሣ። የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠ ሊናገርም ጀመረ፤ ለእናቱም ሰጣት ሁሉንም ፍርኃት ያዛቸውና ታላቅ ነቢይ በእኛ መካከል ተነሥቶአል ደግሞ እግዚአብሔር ሕዝቡን ጎበኘ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።" (ሉቃ 7፥11-17)

ከዚህ በላይ የተጻፈው ቃል እንደሚጠቁመን ኢየሱስ በሥልጣን "አንተ ጎበዝ እልሃለሁ ተነሣ" ሲል እንሰማዋለን አንዳንድ መናፍቃን ኤልያስ ኤልሳዕም እንጂ ሙት አስነሥተዋል አማልክት ልትሉአቸው ነውን? በማለት በብዙ ዕንባ በብዙ ጩኸት ስመ እግዚአብሔርን በመጥራት ያደረጉትን ተአምራት በመለኮታዊ ሥልጣኑ ኃይልን

www.ethiopianorthodox.org

ከሚያደርገው ከኢየሱስ ጋር ሊያወዳድሯቸው ይሞክራሉ። በ1ነገ 17፥17 ላይ የተጻፈውን የኤልያስን ጩኸት አልሰሙምን? ወደ ማንስ እንደጮኸ አላነበቡምን?

"ከዚህም በኋላ የባለቤቲቱ ልጅ ታመመ ትንፋሹም እስኪታጣ ድረስ ደዌው እጅግ ከባድ ነበረ። እርስዋም ኤልያስን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? ኃጢአቴንስ ታሳስብ ዘንድ ልጄንስ ትገድል ዘንድ ወደ እኔ መጥተሃልን? አለችው። ኤልያስም ልጅሽን ስጪኝ አላት ከብብትዋም ወስዶ ተቀምጦበት ወደነበረው ሰገነት አወጣው። በአልጋውም ላይ አጋደመው ወደ እግዚአብሔርም፦ አቤቱ አምላኬ ሆይ ልጅዋን በመግደልህ ይህችን ትቀልበኝ የነበረቺቱን ባልቴት እንዲህ ደግሞ አስጨነቅኻትን? ብሎ ጮኸ በብላቴናውም ላይ ሦስት ጊዜ ተዘረጋበት ወደ እግዚአብሔርም አቤቱ አምላኬ ሆይ የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ ብሎ ጮኸ። እግዚአብሔርም የኤልያስን ቃል ሰማ የብላቴናውም ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች እርሱም ዳነ።" (1ነገ 17፥17-22)

"ኤልሳዕም ወደቤት በገባ ጊዜ እነሆ ሕጻኑ ሞቶ በአልጋው ላይ ተጋድሞ ነበር። ገብቶም በሩን ከሁለቱ በኋላ ዘጋ። ወደ እግዚአብሔርም ጸለየ መጥቶም በሕፃኑ ላይ ተኛ አፉንም በአፉ ዓይኑንም በዓይኑ እጁንም በእጁ ላይ አድርጎ ተጋደመበት የሕፃኑም ገላ ሞቀ ተመልሶም በቤቱ ውስጥ አንድ ጊዜ ወዲህና ወዲያ ተመላለሰ። ደግሞም ወጥቶ ሰባት ጊዜ በሕፃኑ ላይ ተጋደመ ሕፃኑም ዓይኖቹን ከፈተ። ግያዝንም ጠርቶ፦ ይህችን ሱነማዊት ጥራ አለው ጠራትም ወደ እርሱም በገባች ጊዜ ልጅሽን አንሥተሽ ውሰጂ አላት። ገብታም በእግሩ አጠገብ ወደቀች በምድር ላይ ተደፋች ልጅዋንም አንሥታ ወጣች።" (2ነገሥ 4፥32-37)



www.ethiopianorthodox.org

ኤልሳዕ ስንት ጊዜ እንደወደቀ እንደተነሣ ልብ አሉት ይሆን? እስኪ ኤልያስን ይጠይቁት በሥልጣኔ አስነሣለሁ ይላል? ኤልሳዕስ ቢሆን በጉልበቴ በጽድቄ ይላል? አይልም በእግዚአብሔር ኃይል ይላል እንጂ።

ወገኖች ከአምላክ በቀር በሥልጣን የሚናገር፣ የሚፈውስ ኃጢአትን የሚያስተሠርይ ሥነፍጥረትን የሚያገዛ፣ ሙት የሚያስነሣ የለምና ዋናውን እምነታችንን እንዳንረሣ ከመለኮታዊ ሥራው እንማር።

## 5. *ቅዱሳት መጻሕፍት፤*

ቅዱሳት መጻሕፍት የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ምሥክሮች ናቸው። ስለዚህ ማንኛውም ሰው ኢየሱስ ማን እንደሆነ ለማወቅ ቢፈልግ ቅዱሳት መጻሕፍትን በቅድስና፣ በማስተዋል ተመልክቶ ማንነቱን ማወቅና ማመን፣ ወደዘለዓለማዊ ሕይወት መድረስ ይቻላል። ቅዱሳት መጻሕፍት ስለኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት የሚመሠክሩ መሆናቸውን ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ለምሥክርነት ጠቅሷቸዋል። እንዲህ ብሎ "እናንተ በመጻሕፍት የዘለዓለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ እነርሱም ስለእኔ የሚመሰክሩ ናቸው ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም።" (ዮሐ 5፥39) ይህ መለኮታዊ ቃል የሚያስታውሰን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለኢየሱስ የሚመሰክሩ መሆናቸውን ነው። በአንጻሩም የሚከተለውን እንመልከት "እርሱም እናንተ የማታስተውሉ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው።" (ሉቃ 24፥25-27) እንዲሁም "እርሱም ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለእኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው እንዲህም አላቸው፦ ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል በስሙም ንስሐና የኃጢአት ሥርየት ከኢየሩሳሌም

ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል። ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል" (ሉቃ 24፥44-47) አላቸው። በዚህ የመጽሐፍ ክፍል ሦስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ኢየሱስ ልደት፣ ልሕቀት፣ ሕማም፣ ሞት፣ ትንሣኤ፣ ዕርገት እንደመሰከሩና ለዚህም ዓላማ እንደተጻፉ ተገልጿል። ሁሉንም በቅደም ተከተላቸው መሠረት እንዴት እንደ መሰከሩለት እንመልከት፡-

### 5.1 *የሙሴ ሕግ፤*

የሙሴ ሕግ የሚባሉት ኦሪት ዘፍጥረት፣ ዘጸአት፣ ዘሌዋውያን፣ ዘኁልቁ፣ ዘዳግም ሲሆኑ በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለእርሱ የተጻፉትን አልፈን አልፈን እንመለከታለን።

"በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።" (ዘፍ 3፥15-16)

ሴቲቱ ድንግል ማርያም ናት ልጇ ኢየሱስ ነው። አውሬው ደግሞ ዲያብሎስ ነው ይህ ክፍል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚመሰክር ልብ በል

"ሙሴም የዮቶርን የአማቱን የምድያሙን ካህን በጎች ይጠብቅ ነበር። ወደ ምድረ በዳ ዳርቻም በጎችን ነዳ ወደ እግዚአብሔርም ተራራ ወደ ኮሬብ መጣ። የእግዚአብሔርም መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል ታየው። እነሆም ቁጥቋጦው ስለምን አልተቃጠለም? ይህን ታላቅ ራእይ ልይ አለ። እግዚአብሔርም እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደመጣ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከቁጥቋጦው ውስጥ እርሱን ጠርቶ ሙሴ ሙሴ ሆይ አለ እርሱም እነሆኝ አለ ወደዚህ አትቅረብ አንተ



www.ethiopianorthodox.org

የቆምህባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ" (ዘጸ 3፤1-5) እንደተባለ።

የለመለመች ቁጥቋጦ የእመቤታችን (የትስብእት) ምሳሌ እሳት ደግሞ የአካላዊ ቃል ምሳሌ መሆኑን ልብ እንበል በሌላ በኩል ደግሞ "አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል እርሱንም ታደምጣለህ" ተብሎ ተጽፏል። (ዘዳ 18፥17-18 የሐዋ 7፥37-40, ሉቃ 13፥33 ጋር እናገናኙብ)

### 5.2 *ነቢያት ዮሐ 1፥46*

ነቢያት የሚባሉት ደግሞ ስለኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ማርያም መገለጥ የተነበዩና የመሰከሩለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ናቸው። በውስጣቸው ከተጻፉት ጥቂቶቹን ለምሳሌ እንጠቅሳለን።

"ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም ድንቅ መካር ኃያል አምላክ የዘለዓለም አባት የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል ከዛሬ ጀምሮ እስከዘለዓለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም የእግዚአብሔር ቅንዓት ይህን ያደርጋል።" (ት.ኢሳ 9፥6-8) ተብሎ ተጽፏል።

በተጨማሪም በኢሳ 53፥1-2 የተመዘገበውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መመልከት በጎ ነው።

### 5.3 መዝሙራት፤

መዝሙራት የሚባሉት ደግሞ የዳዊት መዝሙራት ናቸው። በመዝሙራት ውስጥ ብዙ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ልደት፣ ልሕቀት፣ ሕማም፣ ሞት፣ ትንሣኤ የተጻፈ አለ። ለምሣሌ ያህል መዝ 21፥16-20 የተመዘገበውን እንመልከት በተረፈ "በዘለዓለማዊ ሕይወት" የተጠቀሰውን ተመልከት። ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ የመንፈስ ቅዱስ ልጁ የሚሆን ጢሞቴዎስ በሕፃንነት እያነበባቸው ያደገባቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት (የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት) ዓላማ ሲገልጽለት "ከሕፃንነትህ ጀምሮ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉ ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃል።" (2ጢሞ 3፤5-16) በማለት ሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት በኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚገኘው መዳን እንደሚመሰክሩ ገልጿል።

### 5.4 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ምሥክርነት፤

"ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ . . . ተጽፏል" ዮሐ 20፥31

"የዘለዓለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።" 1ዮሐ 5፤13 ተብሎ እንደተጻፈ። የተጻፉበት ዋና ዓላማ ለ ምኑበት ሕይወት ሰጪ አምላክ መሆኑን ይመሠክሩ ዘንድ ነው።

## 6. የሙሴ ምሥክርነት፤

ስለኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ከሚመሠክሩት ምሥክሮች መካከል ሙሴ አንዱ ነው። ሙሴ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሥክር መሆኑ እራሱ ጌታ



ተናግሯል። "እኔ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ የሚከሳችሁ አለ እርሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው፤ ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር እርሱ ስለእኔ ጽፎአልና መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?" ዮሐ 5፥45-47 ሙሴም የሚከተለውን ተናግሮ ነበር።

"በአንተና በሴቲቱ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ።" ዘፍ 3፥15

"በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም። የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ የአሕዛብ መታዘዝ ለእርሱ ይሆናል። ውርንጫውን በወይን ግንድ ያስራል የአህያይቱንም ግልገል በወይን ሐረግ ልብሱን በወይን ያጥባል መጎናጸፊያውንም በወይን ደም ዓይኑም ከወይን ይቀላል ጥርሱም ከወተት ነጭ ይሆናል።" (ዘፍ 49፥10-12)

"አምላክህን እግዚአብሔርን በኮሬብ ስብሰባ ተደርጎ በነበረበት ቀን፣ እንዳልሞት የአምላኬን የእግዚአብሔርን ድምፅ ደግሞ አልስማ፣ ይህችን ታላቅ እሳት ደግሞ አልይ ብለህ እንደለመንኸው ሁሉ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል እርሱንም ታደምጣለህ እግዚአብሔርም አለኝ የተናገሩት መልካም ነው። ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ።" (ዘዳ፤ 15-18) በማለት ነበር የመሠከረው።

ስለዚህ "ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ ከሙታንም አንዱ እንኳ ቢነሣ አያምኑም አለው።" ሉቃ 16፥21 የተባለው እንዳይደርስብን እንመን። ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ክፍሎች ስለኢየሱስ ክርስቶስ አድኅኖት፣ ነቢይነት ማንነት የሚጠቁሙ በመሆናቸው ሙሴ ምን ያህል

www.ethiopianorthodox.org

ተቀዳሚ ሰማዕት (ምሥክር) እንደሆነ እንገነዘብባቸዋለን አዎን የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሥክር ነው።

## 7. ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፤

በወንጌል የተነገረውን እንመልከት

"ፈሪሳውያንም አንተ ስለራስህ ትመሠክራለህ ምሥክርነትህ እውነት አይደለም አሉት። ኢየሱስ መለሰ አላቸውም፡- እኔ ስለራሴ ምንም እንኳ ብመሠክር ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁና ምሥክርነቴ እውነት ነው፤ እናንተ ግን ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አታውቁም። እናንተ ሥጋዊ ፍርድን ትፈርዳላችሁ። እኔ በአንድ ሰው ስንኳ አልፈርድም። የላከኝ አብ ከእኔ ጋር ነው እንጂ ብቻዬን አይደለሁምና እኔ ብፈርድ ፍርዴ እውነት ነው። የሁለት ሰዎችም ምሥክርነት እውነት እንደሆነ በሕጋችሁ ተጽፎአል። ስለራሴ የምመሠክር እኔ ነኝ የላከኝም አብ ስለእኔ ይመሠክራል።" (ዮሐ 8፥14-19) በማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ስለራሱ እንደመሰከረ እናነባለን። ምናልባት አንዳንድ ሰዎች የፈሪሳውያንን ጥያቄ በመድገም እንዴት ስለራሱ ይመሠክራል በማለት ይጠይቁ ይሆናል። እኛ ግን እርሱ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው "ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም . . ." (ዘኁ.23፥19) እንላለን የመጣውም ስለእውነት ሊመሠክር መሆኑን አንዘንጋ "ጲላጦስም እንግዲያ ንጉሥ ነህን? አለው። ኢየሱስ መልሶ፡- እኔ ንጉሥ እንደሆንሁ አንተ ትላለህ እኔ ለእውነት ልመሠክር ስለዚህ ተወልጃለሁ። ስለዚህ ወደዓለም መጥቻለሁ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው። ጲላጦስ እውነት ምንድር ነው? አለው።" (ዮሐ 18፥37-38) እውነት ማን እንደሆነ ደግሞ "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።"(ዮሐ 14፥6) ተብሎ የተጻፈውን ቃል ልብ እንበል።



www.ethiopianorthodox.org

ክርስቲያን ሆይ ኢየሱስ እውነተኛ አምላክ ነውና ስለሱም ሆነ ለአንተ የተናገረውን ልብ ብለህ ስማ የእግዚአብሔር ቃል "የእግዚአብሔር ልጅ እንደመጣ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደሰጠን እናውቃለን እውነተኛ በሆነው በእርሱ አለን እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው። ልጆች ሆይ ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ" ብሏል 1ዮሐ 5፥20-21 አዎን ሐሰትን ይናገር ዘንድ እርሱ ክብር ፈላጊ ሰው አይደለም ሰው እንጂ መዋሸቱ የከበረ መስሎት ነው?

## 8. ሐዋርያት፤

ስምንተኛዎቹና የመጨረሻዎቹ ምሥክሮች ቅዱሳን ሐዋርያት ኢየሱስን በዓይናቸው አይተውታል በጆሮአቸው ሰምተውታል በእጃቸው ዳስሰውታል ስለዚህ ለእርሱ ሊመሠክሩ የተገባቸው ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ "ስለሕይወት ቃል ከመጀመሪያ የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻንም የዳሰሱትን እናወራለን።" ብሏል 1ዮሐ1፥1-2 ስለዚህ ኢየሱስ ክርስቶስም "ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ እርሱ ስለእኔ ይመሠክራል እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሠክራላችሁ።" (ዮሐ 15፥26-27)

"እናንተ ለዚህ ምሥክሮች ናችሁ።" ሉቃ 24፥48

"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምሥክሮቼ ትሆናላችሁ" (ሐዋ 1፥8) በማለት ተናግሯል።

እኛም ክርስቲያኖች ልንመሠክር ይገባናል ባንመሠክር በሰሙ ብናፍር የሰው ልጅ ኢየሱስ ሁለተኛ ሲመጣ ያፍርብናል "ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሠክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው አባቴ ፊት እመሠክርለታለሁ" ብሏል ማቴ 10፥32-33

እንግዲህ ወገኖች ሆይ በሁለት ወይም በሦስት ምሥክር ነገር እንደሚጸና ተጽፏል (ዘዳ 19፥15-21, 1ጢሞ 5፥19)

እኛ ግን ከላይ ከተራ ቁጥር 1-8 የተዘረዘሩትን ምሥክሮች በመቀበል በኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ላይ በቂ ጥናት ልናጠና ከጥርጥርም ልንድን በኦርቶዶክሳዊ እምነታችንም ልንጸና ይገባል። ለኢየሱስ ክርስቶስ የማንነት ምሥክሮች እስከዚህ ከተመለከትን ከዚህ በመቀጠል ኢየሱስ ማነው? የሚለውን ጥናት እናጥናና ከሌሎች መናፍቃን ትምህርት ርቀን ስለኢየሱስ እውነተኛውን እንወቅ።

ለዚህ ጥያቄ መልስ የሚሰጡትን ስምንቱን ምሥክሮች በቅደም ተከተል መመመልከታችንን ሳንዘነጋ እነዚህ ስምንቱ ምሥክሮች ማን ነው እንዳሉት ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን።

1. *ስሙ*

ይህ ኢየሱስ የተባለው ስም አማኑኤልን ጨምሮ ስመ ተጸውኦ (የመጠሪያ ስም) ይባላል።

*የስሙ ትርጉም*

ኢየሱስ ማለት ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙ አዳኝ መድኃኒት ሕይወት ቤዛ መቤዠው ማለት ነው። ስምንቱም ስመ ተጸውዖ ነው። ስሙን የነገረን መጋቤ ሐዲስ ቅ/ገብርኤል ነው። በቅድሚያ የነገራት



ለእናታችን ለቅድስት ድንግል ማርያም ነው። እንዲህ ብሎ "ስሙን ኢየሱስ ትይዋለሽ" (ሉቃ 1፥31) ለሁለተኛ ጊዜ የተነገረው ደግሞ ለቅ/ዮሴፍ ነው "ወትሰምዮ ስሞ ኢየሱስሃ ማለት ስሙንም ኢየሱስ ትለዋለህ" ብሎ ማቴ 1፥21-25 መጨረሻም በቤተ ግዝረት ለሁሉ ታወጀ እንዲህ ተብሎ "ስሙ ኢየሱስ ተባለ" (ሉቃ 2፥21) ስሙ አዳኝነቱን ያመለክታል። አድኅኖቱም እንደምድራውያን የጤና ባለሙያዎች አይደለም። ደዌ ሥጋን ደዌ ነፍስን ይፈውሳል፣ መድኃኒት ከውጭ አያሻውም መድኃኒቱ እርሱ ራሱ ነው፣ በሙያው ላይ ጥናት አያስፈልገውም፣ ዕውቀቱ የባሕርዩ ነው፣ መድኃኒት የሚያስወስድበት መርፌ አያሻውም፣ ሲፈውስ አይታይም፣ ገንዘብ አይጠይቅም፣ መዳን ለሚፈልጉ ሁሉ በቸርነቱ እንዲያው ይሰጣል (ኤፌ 2፥8, ኢሳ 55፥2-5)፣ የሕመምተኞችን ድካም ስለሚያውቅ ወደ እነርሱ መጥቶ ይፈውሳቸዋል (ሉቃ 19፥10, ዮሐ 1፥12) የሚፈውሳቸው ሁሉ ተረፈ ደዌ ስለሌላቸው ወዲያውኑ ይቆማሉ። (ሉቃ 4፥38-39, ዮሐ 5፥1-15) ስሙ ኢየሱስ ተብሎ እንደስሙ የሚሠራ የተሰየው በግ ይመስገን።

ኢየሱስ የሚለው ስም በብሉይ ኪዳን እንደሌሎቹ ስሞች በግልጽ ባይጠቀስም የእርሱ ምሳሌ ሊሆኑ ስሙን (ኢየሱስ የሚለውን) የተሸከሙ ብዙዎች ነበሩ። ለምሳሌ ኢያሱ የተባለው ስም (ኢያሱ 1፥1-8 2ዜና 24፥11) ሆሴዕ የሚለው ስምም ኢየሱስን ያመለክት ነበር። ኢያሱ የኢየሱስ ክርስቶስን ስም የተሸከመ ትንቢታዊ ሰው እንደነበረ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንት የሚሉትን እንስማቸው።

## *የሁለቱ ሊቃውንት አተረጓጎም*

1. *ቅዱስ ቄርሎስ የእስክንድርያ ሊቀጳጳስ፦* ሊቁ ስለመልከጼዴቅ በሚናገርበት አንቀጽ መልከጼዴቅ የክርስቶስ ምሣሌ ነበር። መልከጼዴቅ ማለት . . . ንጉሠ ሰላም ንጉሠ ጽድቅ ማለት ነው።

www.ethiopianorthodox.org

መልከጼዴቅ በመባሉ በባሕርይ ንጉሠ ሰላም የሆነ አይደለም። ለንጉሠ ሰላም ለንጉሠ ጽድቅ ለኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ስመ መንግሥቱን ተሸክሞ ቆየ እንጂ ካለ በኋላ ስለ አውሴ ኢያሱ መባል አውሴ የነበረ ስሙ ኢያሱ ተባለ ኢያሱ ማለት የሰዎች ሁሉ መድኃኒት ማለት ነው። ኢያሱ በባሕርዩ አዳኝ አልነበረም "ጸዋሬ ስም" በስም ብቻ መድኃኒት ተባለ እንጂ መልከጼዴቅ ስመ መንግሥቱን እንደተሸከመ ኢያሱም የአዳኝነት ስሙን ተሸክሞ ኖረ በባሕርይ አዳኝ መባል ለኢየሱስ ብቻ ይገባዋል ብሏል። (ተረፈ ቄርሎስ ጉባኤ 23 ገጽ 465 ይመልከቱ)

2. *ዮሐንስ አፈወርቅ፡-* ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅም ሙሴ አውሴን ኢያሱ በማለቱ በዘዳ 18፥16-18 ከተጻፈው የትንቢት ቃል ጋር የሚዛመድ ትንቢት እንደተናገረ ጠቁሞ ኢያሱ ፀሐይ ያቆመው ጠላትን ያሸነፈው ከነዓንን ለሕዝበ እሥራኤል ያወረሰው ኢየሱስ የሚለውን ስም ኢያሱ ተብሎ ስለተቀዳጀ ነው ብሏል።

ኢያሱ የክርስቶስ ምሳሌ ነውና ኢያሱ "ፀሐይ ጨረቃን አቆመ" ብሏል (ተግሣጽ ዘዮሐንስ አፈወርቅ ገጽ 525 ተግ 27 ይመልከቱ) ከሁለቱ ሊቃውንት ጋር የሀገራችን ድርሰትም ይስማማል "አክሊለ ስምከ እንዘ ይትቄጸል በርእሱ አኅጉረ ፀር ወረሰ ኢያሱ ስምህ አክሊልን በመቀዳጀቱ ኢያሱ የጠላትን አገር ወረሰ" የሚለው። (መልክዐ ኢየሱስ)፤ በትንቢት የአዳኝነት ስሙን የተሸከመው ኢያሱና ኢየሱስ ክርስቶስ በብዙ መልኩ ይመሳሰላሉ፤ ለምሳሌ፡- እሥራኤል ዘሥጋ በኢያሱ የመከራውን ጉዞ ጨርሰው ዮርዳኖስን እንደተሻገሩ እሥራኤል ዘነፍስም (ክርስቲያኖች) በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ከግብጽ ኃጢአት ኑሮ ከፈርኦን ዲያብሎስ እጅ ነፃ ወጥተዋል።



እሥራኤል ዘሥጋ በኢያሱ የአርባ ዘመን ነውራቸው እንደወደቀ ምዕመናንም በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ነውራቸው ተንከባሎላቸዋል። እስራኤል ዘሥጋ የኢያሪኮ ግንብ ፈርሶላቸው ምድረ ርስትን እንደወረሱ ምእመናን የኃጢአታችን ግንብ በመስቀሉ ወድቆልን መንግሥተ ሰማያት የመግባታችን ምሳሌ ነው። በተጨማሪ ስለ ኢያሱና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያነጻጽረውን ይመልከቱ።

በስሙ የተጠራን እኛም የዚህ ስም ጥቅሙ ሊገባን በስሙ ልንጸልይ (ዮሐ 14፥13) አጋንንትን ልንዋጋ ይገባናል በስሙ ልናፍር አይገባንም እርሱ በመንግሥቱ በመጣ ጊዜ እንዳያፍርብን (ማቴ 10፥32) ሐዋርያት ኃይል ያደረጉበት የተገረፉለት ስም ይህ ነው (የሐዋ 3፥4-5, 40-41) ጉልበት ሁሉ ለዚህ ከስሞች ሁሉ በላይ ለሆነው ስም ሊንበረከክ ይገባዋል። (ፊል 2፥10)

www.ethiopianorthodox.org

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ኢየሱስ ማነው? (ማንነቱ)

### 1. ክርስቶስ ነው፤

ኢየሱስ ማነው ብለው ለሚጠይቁን ሁሉ እኛ ኦርቶዶክሳውያን ተቀዳሚ መልሳችን እንደ ቅ/ጴጥሮስ ክርስቶስ ነው የሚል ይሆናል። በዚህ መልሳችን ከአይሁድ እንለይበታለን።

የአይሁድ ትልቁ ክሕደታቸው "ዓመፃን ይጨርስ፣ ኃጢአትንም ይፈጽም በደልንም ያስተሰርይ ዘንድ፣ የዘለዓለም ጽድቅን ያገባ፣ ራዕይንና ትንቢትን ያትም፣ ቅዱሰ ቅዱሳንም ይቀባ ዘንድ በሕዝብህና በቅድስት ከተማህ ላይ ሰባ ሱባዔ ተቀጥሮአል። ስለዚህ እወቅ አስተውልም፤ ኢየሩሳሌምን መጠገንና መሥራት ትእዛዙ ከሚወጣበት ጀምሮ እስከአለቃው እስከ መሢሕ ድረስ ሰባት ሱባዔና ስድሳ ሁለት ሱባዔ ይሆናል እርስዋም በጭንቀት ዘመን ከጎዳናና ከቅጥር ጋር ትሠራለች። ከስድሳ ሁለት ጊዜ ሰባትም በኋላ መሢሕ ይገደላል፣ በእርሱም ዘንድ ምንም የለም። የሚመጣውም አለቃ ሕዝብ ከተማይቱንና መቅደሱን ያጠፋሉ። ፍጻሜውም በጐርፍ ይሆናል፣ እስከ መጨረሻም ድረስ ጦርነት ይሆናል። ጥፋትም ተቀጥሮአል፤ እርሱም ከብዙ ሰዎች ጋር ጽኑ ቃል ኪዳን ለአንድ ሱባዔ ያደርጋል በሱባዔውም እኩሌታ መሥዋዕቱንና ቁርባኑን ያስቀራል። በርኩሰትም ጫፍ ላይ አጥፊው ይመጣል እስከ ተቀረጠውም ፍጻሜ ድረስ መቅሠፍት በአጥፊው ላይ ይፈስሳል።" (ት/ዳንኤል 9፥24-27) ተብሎ የተነገረውን አለመቀበላቸውና ኢየሱስን ክርስቶስ ነው ብሎ ላለማመን መጻሕፍቶቻቸውን መቀንጸላቸው ነበር። በዚህ ክሕደታቸውም ተጎዳበት እንጂ አልተጠቀሙበትም።



አይሁድ ኢየሱስን ክርስቶስ አይደለም በማለት በቅንአት ሐሳብ ተነሣተው መሢሁን ላለመቀበል መጻሕፍቶቻቸውን እንዴት እንደቆነፀሉ እና ሕዝባቸውን ሕይወቱ ከሆነው ከአምላኩ እንደለዩት ሰፊ ማብራሪያ የሰጡትን የሊቁን የኪዳነ ወልድ ክፍሌን ሐሣብ አንባቢ ተመልክቶ ይጠቀምበት ዘንድ ሙሉ ቃሉን "መዝገበ ፊደል" ከተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ ጠቀስ አድርገን አቅርበነዋል አንባቢ አሣዛኙን ታሪክ ይመልከት።

ከክርስቶስ በፊት የነበረው ዘመን ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ፣ ዘመነ ብሉይ ይባላል። ከክርስቶስ ወዲህ ያለው ዘመን ዓመተ ምህረት፣ ዓመተ ሥጋዌ ዘመነ ሐዲስ ይባላል ይኸውም ዘመነ መሲሕ ማለት ነው መላው ባንድነት ሲደመርና ሲጠቀለል ዓመተ ዓለም መዋዕለ ዓለም ይባላል። ኢትዮጵያ ዘመነ ብሉይን 5,000 ከ500 ወይም 5,500 ማለቷ ከጥንታዊው ጽርእ የተቀዳ ከዮናኒ የተመለሰ መጽሐፈ ኦሪቷን ተከትላ ነው።

ኦሪት በዘመነ ብሉይ 3 ጊዜ ተካክሎ ተጥፎ በ3 ስሞች ተጠርቷል መጀመሪያ ሙሴ የጻፈው ኦሪት ሌዋውያን ተብሏል። 2ኛ በስልምናሶር ዘመን ምናሴ ካህነ ቤቴል ለሰማርያ ሕዝብ የጣፈው ኦሪት ሳምራውያን ተብሏል። እነሂም አሕዛብ ናቸው (1ኛ ነገ 17፥24-30) 3ኛ በበጥሊሞስ ዘመን ሰብዓ ሊቃናት ከዕብራኒ ወደ ዮናኒ የመለሱት በስማቸው ኦሪት ሊቃናት ተብሏል (የካ.8.ስንክ) ከዚህ በኋላ አይሁድ በዘመነ ሐዲስ ኦሪት ነቢያትን ለመቃወም በእግዚአብሔርና በመሢሁ ላይ በጠላትነት ተነሥተዋል።

ኦሪት ነቢያት የሰበኩት እርግጡ የመሢሕ አመጣጥ ለማዳንና ለመፍረድ በትኅትና እና በልዕልና በዕዋልና በደመና 2 ጊዜ ሲሆን የትኅትናውን አመጣጥ ፊተኛውን ክደው ኋለኛውን ብቻ የልዕልናውን ስላመኑ ኋላም እነዚሁ ተሳስተው ከመሢሕ በፊት በሚመጣው በሐሣዊ መሢሕ የሚያምኑ ሐሣውያን ነቢያተ ሐሰት ስለሆኑ የመሢሕን



www.ethiopianorthodox.org

መንግሥት ሥጋዊ ምድራዊ አስመስለው መሚሑንም ሥግው ቃል ያይደለ ዕሩቅ ብዕሲ ብለው ከእውነተኛው አምልኮ ከእግዚአብሔር መንግሥት ከአብርሃም በረከት ወጥተው በኦሪት መርገም ተጨልጠውና ተገርኝተው ወደ ሰይጣን መንግሥት ሂደዋል (ዮሐ 8፥44, ራዕ 9) የአዳም ኃጢአት እንደ ኩብሽና እንደ ቂጥኝ ወርሶት በሔዋን እባብ መርገዘ ተወግቶ ሁለንተናው ቆስሎ ተበላሽቶ ውሾች አጋንንት የሚልሱት ይህ በሽተኛ ዓለም ከጥንቱና ከመሠረቱ ካባቱ ከአዳም ከናቱ ከሔዋን ጀምሮ ፈጣሪው የሰጠው የመድኃኒት ተስፋ ስላለው ስሙ ከግብሩ ተስማምቶለት ተባብሮለት ኢየሱስ አማኑኤል ተብሎ በሙሴ እባብ አምሳል ተሰቅሎ ከሰማይ እባብ ከዲያብሎስ ሕምዝ ከሠራዊቱ መርዝ የሚያድን ሰማያዊ ንጉሥ ሐኪምና ፈውስ የማይሻ መስሏቸው የእንቅፋትና የማዕዘን ድንጋይ በተባለው ክርስቶስ ትህትና በፍጹም ውርደቱ ጨርቅ አጠርቅሞ ግንድ ተሸክሞ በመታየቱ በመስቀሉ ተሰናክለው ትንሣኤውንም አስተባብለው እውነተኛውን መሚሕና መድኅን ላለመቀበል የመሚሕን ዘመን ከዘመናቸው ለማራቅ መሚሑም ዘመኑም ሌላ ነው፤ ገና ወደፊት ነው ይህ ዛሬ በኛ ዘመን ንጉሠ አይሁድ ተብሎ ዓለም ሁሉ የተከተለው እኛ ግን ሰቅለን የገደልነው የናዝሬቱ ኢየሱስ ምንም ከዳዊት ዘር ቢወለድ ለኛ ተገዛ እንጂ በኛ ላይ አልነገሠምና መሚሕ አይደለም ለማለት እግዚአብሔር በሙሴ እጅ ላባቶቻቸው ለሌዋውያን የሰጠውን ኦሪት በዘመኑ አበው ምክንያት ከኦሪት ዘፍጥረት ሁለቱን ምዕራፍ (5 እና 11) ስላበጠሉት (ስለቆረጡት) ስሙ ተለውጦ ኦሪተ አይሁድ ብጡል ተብሏል።

ኢዮርብዓም ዐሥሩን ነገድ ከእግዚአብሔርና ከኢየሩሳሌም ለማራቅ በዳንና በቤቴል ተራራ 2 የወርቅ እንቦሶችን አማልክት ብሎ እንዳቆመ አይሁድም ግብዝ ሕዝባቸውን ከእውነተኛው መቅደስ ከክርስቶስና ከቤተ ክርስቲያኑ ለማራቅ በኦሪትና በነቢያት መጽሐፍ የንባብ ግልፎ (ጣኦት) አቁመዋል።



አለመስታዎት ዐይንን በዐይን ማየት እንዳይቻል አለመሚሕም መምህርነት የብሉይ ኪዳንን ትርጓሜ አካቶ ፈጽሞ ማወቅ መረዳት ርግጡን ማወቅ ለማንም ለማን አይቻልምና ከዚህ የተነሣ የክርስቶስ ደቀመዛሙርት ሐዋርያት አርድዕት ይልቁንም የኦሪት ትምህርት አበጋዞች የብሉይ የሐዲስ መሐንዲሶች እነ ጳውሎስ እነ እስጢፋኖስ እነዚህን የመሰሉ ሁሉ ሱባዔ ትውልድ ከሔኖክ ሱባዔ ዘመን ከዳንኤል ሱባዔ እየሰጡ ትውልዱን ከዘመን ትንቢቱን ከመድኅን እያስማሙና እየተረጐሙ ኦሪትን በፋና በአጋር በዓመት ወንጌልን በዐሐይ በሣራ በእመቤት ኢየሱስን በይስሐቅ በአብርሃም መሥዋዕት እየመሰሉ ወማኅለቅቱሰ ለጽድቀ ኦሪት አሚን በክርስቶስ፤ እስመ ጽላሎታ ይእቲ ኦሪት ለእንተ ትመጽእ ሠናይት። ኦሪትሰኬ መርሐ ኮነተነ ለኀበ ክርስቶስ እንከሰ ኢንፈቅድ መርሐ እያሉ በክርክርና በሙግት ወዲህም በአምላካዊ ሐይል በታምራት በ2 ወገን የማይገፉ የማይሸነፉ የብሉይ ጀግኖች የሐዲስ አርበኞች ስለ ኾኑባቸው ካርባ የሚበዙ አይሁዶች እስጢፋኖስና ያዕቆብን ደብድበን እንደገደልን ጳውሎስን ሳንገድል እህል ውሃ እንዳንቀምስ ብለው ከተማማሉ በኋላ እርሱን ለብቻው ማግኘትና መግደል ቢሳናቸው ሥጋዊ ጦራቸው የቈጣቸው ፍሬ የመሐላቸው ሰይፍ በስለቱና ባንደበቱ ወደ መጽሐፍ ተመልሷል።

"በሸንጐ ቢረታ ከቤት ሚስቱን መታ" እንደሚሉት ሁሉ ከኀፍረትና ከብስጭት ከቁጣ ብዛት የተነሣ ወንጌልን ያጠፉ ኦሪትን ያሰፉ መስሏቸው ሐዋርያት የሚያጠቅሷቸውን ደረቅ ትንቢትና ሱባኤ ራዕይ ያላቸውን የክርስቶስን አምላክነትና ሰውነት ድካሙን ኃይሉን መከራ መስቀሉን በሕማሙና በሞቱ የዓለም መድኃኒት መሆኑን እንደ ቅዱስ ወንጌል ገልጠው አፍርጠው የሚናገሩትን ቃላቸው ከብሉይ ንባብ የተለየ ፍፁም ደረቅ ሐዲስ ስለሆነ ከቁጥር ከቀመር ሳይገቡ ለምስክርነት እንደዓ ይን ብሌን እንዳደራ ምናን በፍጹም ጥንቃቄ ተጠብቀው በቤተ መቅደስ ይኖሩ የነበሩትን የብሉይን አዋልድ ሁሉ በሕዝቅኤል መቅድም እንደ

www.ethiopianorthodox.org

ጣፍነው ጭራሽ ከዕብራይስጥ ዕልም ድርግም አድርገው አጠፏቸው ይኸውም በሐዋርያት ጥቅስ ይታወቃል (ማቴ 27፥9, ይሁ 14፥15)።

ከኦሪት ሁለቱን ምዕራፍ፡ (ዘፍ፡ 5፥3-31, 11፥7-26) ለዋውጠው ገላብጠው ዘመነ አበውን አፋለሱት አዳም ሴትን በ230 ወለደ ያለውን በ130 አሉት። እንዲህ እያሉ ሴት ሄኖስን በ205 ያለውን በ105 አሉት። እንዲህ እያሉ መቶ መቶውን ሰርቀው ከፊት ወደኋላ እያዞሩ ከድኅሩና ከድምሩ ጋር ጥፈውታል የፋቁትም 300 ዓመት አለ። ከትውልዱም አንዱን ሁለንተናውን ቃይናንን በጭራሽ ፍቀው ከአዳም እስከ አብርሃም 1,040 ዓመት አጉድለዋል፤ በግዕዙና ባማርኛው ኦሪት ተመልከት። ኦሪተ አይሁድን የተቀበሉ ከአዳም እስከ ክርስቶስ 4ሺህ ያህል የሚሉበት ምክንያት ይህ ነው ኦሪታችን ከሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ ከጥንታዊው ጽርእ መቀዳቱን አስቀድመን ተናግረናል። ስለዚህ እናትና ልጁን አንድ ወገን ኦሪተ አይሁድን አንድ ወገን አድርገን ልዩነታቸውን እስከ መጨረሻ ዘርዝረን ደምረን እናሳያለን።

## ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 5 እና 11

| (ኦሪተ ሊቃ) | (ኦሪት አይ) |
|---|---|
| ቁ.3 አዳም ሴትን በ230 | በ130 |
| ቁ.6 ሴት ሄኖስን በ205 | በ105 |
| ቁ.9 ሄኖስ ቃይናንን በ190 | በ90 |
| ቁ.12 ቃይና መላልኤልን በ170 | በ70 |
| ቁ.15 መላል ያሬድን በ165 | በ65 |
| ቁ.18 ያሬድ ሔኖክን በ162 | በ162 |
| ቁ.21 ሔኖክ ማቱሳላንበ165 | በ65 |
| ቁ.25 ማቱሳላ ላሜህን በ187 | በ187 |
| ጽርኡ ግን 167 ይላል | |
| ቁ.28 ላሜህ ኖኅን በ182 | በ182 |
| ጽርኡ ግን በ188 ይላል | |
| ቁ.32 ኖኅ ሴምን በ500 ዓ.ወ | በ500 |
| ቁ.10 ሴም አርፋክስድን በ100 | በ100 |

| (ኦሪተ ሊቃ) | (ኦሪት አይ) |
|---|---|
| ቁ.12 አርፋክ ቃይናን በ135 | ፍሑቅ (ጩርሶ |
| ቁ.13 ቃይና ሳላህን በ135 | ተፍጿል) |
| ቁ.14 ሳላህ ዔቦርን በ130 | በ35 |
| ቁ.16 ዔቦር ፋሌግን በ134 | በ30 |
| ቁ.18 ፋሌግ ራግውን በ130 | በ34 |
| ቁ.20 ራግው ሴሩግን በ132 | በ30 |
| ቁ.22 ሴሩግ ናኮርን በ190 | በ32 |
| ቁ.24 ናኮር ታራን በ29 ጽርኡ በ179 ይላል | በ20 |
| ቁ.27 ታራ አብርሃምን በ100ዓ ጽርኡ ግን በ70 ይላል | |
| ድሙር ከአዳም እስከ አብርሃም 3 ሺ.ህ ከ386 | |
| | 10637 |



ጽርኡ ከግዕዙ 26 ዓመት ያተርፋልና 26ን ከ86 ቢጨምሩ 3ሺህ ከ412 ዓመት ይሆናል። ኦሪተ አይሁድ ያጎደለው እንደ ግዕዙ ሺ 749። እንደ ጽርኡ ግን ሺ 775 ነው። እግዚአብሔር አስቀድሞ መጻሕፍቱን ወደ ጽርእ ቋንቋ ባያሸሽ የአይሁድ ክፋት የኦሪታቸው ብጡልነት እንዲህ ፈፅሞ ባልታወቀም ነበር። (ተረት ስለበቅሎ ክፋት. . . እግዚአብሔር ባወቀ ሰማዩን አራቀ።) አይሁድ ግን በሕይወታቸው አበጋዘ በክርስቶስ ትንሳኤ ለመቃብሩ ጠባቆች ብዙ ገንዘብ ደፍተው ሐዋርያት አርድእት የተባሉትን 12ቱን አንቅዕተ ሕግና 70ውን የወንጌል በቀልት እንዳስተባበሉ በዚህ ደግሞ 70 ሊቃናትን ያስተባብላሉ (ማቴ 28፤11-15) የሳምራውያንም ኦሪት በዘመነ አበው ቍጥር ከሰብዓ ሊቃናት ትርጓሜ ከኦሪተ ጽርእ እንጂ ብጡል ከተባለው ከኦሪተ አይሁድ አይገጥምም" መዝገበ ፊደል ዘኪዳነ ወልድ ክፍሌ።

እኛ ክርስቲያኖች ግን ኢየሱስን ክርስቶስ ነው ብለን በማመናችን የቅዱሳት መጻሕፍትን ምሥክርነት ከመቀበላችንም በላይ ጸጋና ክብር አግኝተናል። ኢየሱስን ክርስቶስ ነው ብሎ ለማያምን ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃችን የሚከተለው ነው።

"ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛ ማነው? አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም፤ በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው" (1ዮሐ 2፥22-23) ከቅ/ጴጥሮስም የምንሰማው "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ" (ማቴ 16፤16)በማለት እውነቱን ሲናገር ነው። ይህ ቅዱስ አባት በሐዋርያት ሥራ ላይም "እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ።" (የሐ.ሥራ2፥36) ብሏል "አደረገው" ማለት ግን የነሣውን የሰው ልጅ ባሕርይ ለመግለጥ ነው። ማርታም "አዎን ጌታ ሆይ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

ልጅ እንደሆንህ እኔ አምናለሁ" (ዮሐ 11፥27) በማለት ነበር የተናገረችው መጽሐፍ ቅዱስም ከተጻፈባቸው ዓላማዎች አንዱ ይህን እንድናምን ነበር "ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀመዛሙርቱ ፊት አደረገ፣ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።" (ዮሐ 20፥30-31) ሐዋርያውም ስሙን ሲጠራ ስለራሱም ሲናገር "በክርስቶስ ኢየሱስ ስላመናችሁ" (1ቆሮ 1፥4) በማለት ነበር።

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ክርስቶስም ኢየሱስ ነው ማንኛውም ክርስቲያን ልብ ሊለው የሚገባው ነገር ኢየሱስ የሚለው ስም ቋሚ መጠሪያ ሲሆን ክርስቶስ የሚለው ደግሞ ማንነትን የሚገልጽ ስመ ተቀብኦ ነገረ ሥጋዌን የሚገልጽ ስመ ሥጋዌ (የመዐርግ ስም) መሆኑን ነው። እንደዚህ ያለውን ሃይማኖታዊ ቃል በምሳሌ መግለጽ ይቸግራል። ምክንያቱም "እስመ ምሳሌ ይውህድ እም አማን" እንደተባለ በሊቁ ምሳሌ እውነተኛውን ነገር የማይተካና ሙሉ በሙሉ የማይገልጸው በመሆኑ ነው። ቢሆንም ምሥጢሩን ለማቅለል ሳይሆን የአንባቢን አእምሮ ወደ እውነቱ ለማቅረብና ለማገገ ነው። ነገሩን በምሳሌ ግልጽ ለማድረግ አንድ ለምሳሌ አበበ የሚባል ሰው ቢኖር መጠሪያ ስሙ (ስመ ተጸውኦ) አበበ ነው። ነገር ግን ቢካን ዲያቆን፣ ቢቀስስ ቄስ፣ በዶክትሬት ቢመረቅ ዶክተር ሊባል ይችላል። ከላይ የተጠቀሱት ዲያቆን ቄስ ዶክተር የተባሉት ስሞች የመዐርግ ስሞች እንደ ስመ ተቀብኦ ናቸው (ስመ ተቀብኦ ይባላሉ)። እንደዚሁ ሁሉ ኢየሱስ ማለት አበበ ማለት ቢሆን ክርስቶስ ማለት ደግሞ ቀሲስ እንደማለት ነው። ነገር ግን ክርስቶስ የሚለው ቃል ትርጉም በግሪክ የተቀባ መሢሕ ማለት ነው። ስምነቱም ስመ ተዋሕዶ እንደሆነም ሊቃውንት ይናገራሉ። እንዲህ ብለው "አኮ መናፍትው እስምዮ ለቃለ እግዚአብሔር ክርስቶስ ዘእንበለ ትስብዕት ወኢለትስብዕት ዘእንበለ መለኮት ክርስቶስሃ ይሰመይ" (ሃ. አበው)



www.ethiopianorthodox.org

## ቤተክርስቲያን ኢየሱስን ክርስቶስ ብላ በማመና ያገኘችው ጸጋ

### 1.1 የእግዚአብሔር ልጅ መሆንን፤

"ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል።" (1ዮሐ 5፥1)

### 1.2 ብፁዕ መባልን፣ ሰማያዊ ሥልጣንን በሲኦል ኃይሎች የማይናጋ መሠረትን አግኝታለች።

"ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።" (ማቴ 16፥16-17) ተብሎ እንደጻፈ። በተጨማሪም ሐሰተኛ ከመሆን የነቢያትን ቃል ከማስተባበል ድናበታለች (1ዮሐ2፥22-23) የዘለዓለምን ሕይወት አግኝታለች (ዮሐ 20፥31)

### 1.3 ከአሸናፊዎቿ በልጣለች፤

"በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን" ሮሜ 8፥27

### 1.4 በሰማያውያንና በምድራውያን በረከት ተባርካለች፤

"በክርስቶስ በሰማያዊ ሥፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።" (ኤፌ. 1፥3)

## 1.5 ቅድመ ዓለም ለቅድስና ተመርጣለች፤

"ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።" (ኤፌ 1፥4)

## 1.6 የእግዚአብሔር ልጅ እንድትሆን ተወስናለች

"በበጎ ፈቃዱ እንደወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን።" (ኤፌ 1፥5)

## 1.7 የበደል ሥርየት አግኝታለች፤

"በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ። በውድ ልጁም እንደ ጸጋው ባለጠግነት መጠን በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት።" (ኤፌ 1፥6-7)

## 1.8 ዓላማዋ ሁሉ በክርስቶስ ተጠቃለለላት፤

"በክርስቶስ ለማድረግ እንደወደደ እንደ አሳቡ የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው።" (ኤፌ 1፥9-11)

## 1.9 ለእግዚአብሔር ምሥጋና ቆማለች፤

"ይኸውም በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ ያደረግን እኛ ለክብሩ ምሥጋና እንሆን ዘንድ ነው።" (ኤፌ 1፥12)



## 1.10 ያጣችውን ርስቷን ተቀብላለች፤

"እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፣ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ታትማችሁ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው።" (ኤፌ 1፥13)

በእምነታችን ጸንተን የእግዚአብሔር ልጅ እንድንሆን እግዚአብሔር ይርዳን።

## 2. የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

ኢየሱስ ማነው ተብለን ስንጠየቅ የምንመልሰው ሁለተኛ መልሳችን ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚል ነው። መጽሐፍ ቅዱሳውያን መረጃዎቹም የሚከተሉትናቸው።

"ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ ከእግዚአብሔር ተወልዶአል ወላጁንም የሚወድ ሁሉ ከእርሱ የተወለደውን ደግሞ ይወዳል።" (1ዮሐ 5፥1)

"ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ" ማቴ 16፥16

"ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ተጽፎአል።" (ዮሐ 20፥31)

"እርሱዋም አዎን ጌታ ሆይ አንተ ወደዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንህ እኔ አምናለሁ አለችው።" (ዮሐ 11፥27)

www.ethiopianorthodox.org

"የዘለዓለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።" (1ዮሐ 5፥13)

ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። በዚህ አንቀጽ ላይ ልብ የምንለው ዐቢይ ጉዳይ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብለን በማመናችን የባሕርይ ልጅነቱንና አምላክነቱን መግለጻችን ነው።

## ቤተክርስቲያን ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ ብላ በማመኗ ያገኘችው ጸጋ

### 2.1 ዓለምን የምታሸንፍበት ኃይል አግኝታለች

"ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማን ነው?" (1ዮሐ 5፥5)

በተጨማሪም ከላይ ያየናቸውን ጸጋዎች አግኝታለች።

### 3. ጌታ ነው (ይባላል)።

ጌታ ማለት ፈጥሮ የሚገዛ የሚመራ የሚመግብ አምላክ ማለት ነው። እናት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤ/ክ ስለኢየሱስ ማንነት ስትጠየቅ የምትመልሰው መልስ እንዲህ የሚል ነው።

"ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ ክርስቶስ - በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን።" (በኒቅያ የ318ቱ ሊቃውንት ጉባዔ) ይህንንም ትምህርት የተቀበለችው ከአዕማደ ቤ/ክ ሐዋርያት ነው። አባታችን ቶማስ "ጌታዬ አምላኬም" (ዮሐ 20፥28) አለ።



www.ethiopianorthodox.org

ማርታም "አዎን ጌታ ሆይ አንተ ወደዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚብሔር ልጅ እንደሆንህ እኔ አምናለሁ" አለች። (ዮሐ 11፥27) ቅ/ጴጥሮስም "እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ" አለ (ዮሐ 2፥36) ቅ/ጳውሎስም "ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሠክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና።" (ሮሜ10፥9)

"ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሠክር ዘንድ ነው።" አለ (ፊልጵ 2፥11)። እንዲሁም ለቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን በላከው ቀዳማዊ መልእክት "ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር ኢየሱስ የተረገመ ነው የሚል እንደሌለ በመንፈስ ቅዱስም ካልሆነ በቀር ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ።" (1ቆሮ 12፥3-4) በማለት መናገሩን ልብ እንበል።

ታሪክ እንደሚጠቁመን የሮማ ቄሣሮች ራሳቸውን እንደ አማልክት እንደ አጋዕዝት ይቆጥሩ ስለነበር ቤተክርስቲያንን በእሳት በአንበሳ በሠይፍ በማስፈራራትና በመግረፍ ኢየሱስ የተረገመ ነው፤ ቄሣር በእርግጥ የአማልክት ዘር ነው እንዲሉ ያስገድዷቸው ነበር፤ በዚህ ጊዜ ቄሣር እንደኔ ሰው ነው። ጣዖቱም ውዱቅ (የተዋረደ) ነው። ኢየሱስ ግን የኔም የአንተም የሁሉም ጌታ ነው በማለት ይቃወሙ ነበር። ስለዚህ አንድ ክርስቲያን ኢየሱስ ጌታ ነው በማለት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የዲያብሎስን ኃይል ይቃወም ስለነበር ሐዋርያው ከላይ ያነበብነውን ቃል አስቀመጠ።

## 3.1 የክብር ጌታ ነው፤ (ይባላል)

“ከዚችም ዓለም ገገሮች አንዱ እንኳ ይህን ጥበብ አላወቀም አውቀውስ ቢሆን የክብርን ጌታ ባልሰቀሉትም ነበር” (1ቆሮ 2፤8) በማለት ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ እንደተናገረ በሰማይ በምድር ጉልበት ሁሉ የሚንበረከክለት በሰማይ በምድር ጉልበት ሁሉ የሚሰግድለት ጌታ ነው።

“ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በዙፋን ላይ በተቀመጠው ፊት ወድቀው ከዘለዓለም እስከዘለዓለም በሕይወት ለሚኖረው እየሰገዱ፡- ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል። እያሉ በዙፋኑ ፊት አክሊላቸውን ያኖራሉ።” (ዮሐ ራዕይ 4፤11)

“በታላቅ ድምፅ የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት ጥበብም ክብርም ብርታትም ምሥጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል አሉ። በሰማይና ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ በረከትና ክብር ምሥጋናም ኃይልም ከዘለዓለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ አራቱም እንስሶች አሜን አሉ። ሽማግሌዎቹም ወድቀው ሰገዱ።” (ዮሐ ራዕይ 5፥12-14) ተብሎ እንደተጻፈ በተጨማሪም “ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሠክር ዘንድ ነው።” (ፊልጵ 2፥10-11) እንደተባለለት የክብር ጌታ ነው።

## 3.2 ሊሰበክ የሚገባው ጌታ ነው፤

“ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደሆነ እንጂ ራሳችንን አንሰብክምና ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን። በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ ያበራ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና።” (2ቆሮ 4፥5-6)



www.ethiopianorthodox.org

## 3.3 የጌቶች ጌታ ነው (ይባላል)፤ ኢየሱስ ጌታ ብቻ ሳይሆን የጌቶችም ጌታ ነው፤

ከዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባው በጸጋ ጌቶች ካደረጋቸው ምድራውያን ጌቶች መለየት ነው። አብ ጌታ ነው ኢየሱስም ጌታ ነው መንፈስ ቅዱስም ጌታ ነው። ነገር ግን ጌትነታቸው አንዲት ናት፤ ኢየሱስ ከሁሉም ተለይቶ ጌታ የሚባለው በሥጋ በተገለጠበት በዘመነ ሥጋዌው ሰዎች ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለውን እኩልነት ክደው ዕሩቅ ብእሲ (ተራ ሰው) ብለውት ስለነበር ጌትነቱን ክደው ስለነበር ጌትነቱን ለመግለጽ ነው የጌቶች ጌታ መሆኑን የሚገልጹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን እንመልከት። ቤተክርስቲያንም አይሁድ ያልተቀበሉትን ጌትነቱን አምልታ፣ አስፍታ የምትሰብከው ስለሷ በደካማ ሥጋ የመጣው የክብር ጌታ መሆኑን ነው።

“በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ የሚል ስም አለው።” (ራዕ 19፥16)

“እነዚህ አንድ አሳብ አላቸው ኃይላቸውንና ሥልጣናቸውንም ለአውሬው ይሰጣሉ። እነዚህ በጉን ይወጋሉ በጉም የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ስለሆነ እነርሱን ድል ይነሣል። ከእርሱም ጋር ያሉ የተጠሩና የተመረጡ የታመኑም ደግሞ ድል ይነሣሉ።” (ራዕይ 17፥13-15)

“ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገለጥ ድረስ ያለ እድፍና ያለነቀፋ ሆነህ ትእዛዙን ጠብቅ ያንም መገለጡን በራሱ ጊዜ ብፁዕና ብቻውን የሆነ ገዥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ያሳያል እርሱ ብቻ የማይሞት ነው። ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም ለእርሱ ክብርና የዘለዓለም ኃይል ይሁን አሜን።” (1ጢሞ 6፥14-16) ይላል ቅዱስ መጽሐፍ።

ክርስቲያን ሆይ! የጌቶች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ከአውሬው ጋር የተመሳጠሩትን ነገሥታት ድል የነሣ ጌታ ተከታዮቹንም ድል የሚያቀዳጅ ጌታ መሆኑን ልብ አልክን? የሰማይ ጌታ የምድር ጌታ የሚታየውም የማይታየውም ጌታ ኢየሱስ መሆኑን ልብ አልክ?

አንባቢ ሆይ! የአንተስ ጌታ ማን ነው? የነፍስህ ጌታ የሥጋህ ጌታ የመንፈስህ ጌታ የአእምሮህ ጌታ የቤትህ ጌታ ማን ነው? በአንተነትህ ላይ የሠለጠነው ጌታህ ገለሙት ነውን? ስካር ነውን? ጣዖት አምልኮ ነውን? የገንዘብ ፍቅር ነውን? "ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።" (ማቴ 6፤24-25) ተብሎ ተጽፏል። አንተነትህን የሚገዛው ማን ነው? ማንንስ መርጠሃል? በእግዚአብሔር ቃል "ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደሆናችሁ አታውቁምን?" (ሮሜ 6÷16) ተብሎ እንደተጻፈ ለምትታዘዝለት ባሪያው እንደሆንህ አታውቅም? እንግዲያውስ ጌታህ የምትታዘዝለት ነውና በሕይወትህ ለማን እንደምትታዘዝለትና ጌታህም ማን እንደሆነ ልብ በል። በሕይወቱ ኢየሱስ ጌታው የሆነለት ሕዝብ ብፁዕ ነው።

እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ኢየሱስ ጌታ ነው የሚለውን ኦርቶዶክሳዊ ትምህርታችንንና አቋማችንን የትናንቱ የፕሮቴስታንት ድንኳን የሰበከልን ይመስል "ኢየሱስ ጌታ ነው" ማለት የባዕድ ልሣን ነው ማለት ግን የስሕተት ስሕተት ነው። በአንድ ጌታ የምታምነውን ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያንን መካድ ታሪኳንም ማበላሸት ነው። ስለዚህ በኦርቶዶክሳዊ ሐሳባችን "ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ - በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን" እያልን እስከሞት ድረስ እንታመን (የኒቅያ ጸሎተ ሃይማኖት)



www.ethiopianorthodox.org

## 4. *እግዚአብሔር ነው።*

ኢየሱስ ማን ነው ብለው ለሚጠይቁ ሁሉ እግዚአብሔር እንደሆነ ልንነግራቸው ያስፈልጋል። ለአብ ለመንፈስ ቅዱስ የሆነው ክብር ሁሉ ለእርሱም አንዳች አይጎድለውም። መጽሐፍ ቅዱስም መለኮታዊነቱን በሚከተሉት መንገዶች ይገልጸዋል።

### 4.1 *በብሉይ ኪዳን ስለእግዚአብሔር (በእግዚአብሔር ስም) የተነገሩት ትንቢቶች በኢየሱስ በመፈጸማቸው እግዚአብሔርነቱን ይገልጻሉ፤*

"እንዲህ ይሆናል የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል። እግዚአብሔርም እንደተናገረ በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም መድኃኒት ይገኛል። ደግሞም እግዚአብሔር የጠራቸው፣ የምሥራች የሚሰበክላቸው ይገኛሉ።" (ኢዩ. 2÷32) "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል" (የሐ ሥራ 2÷21) "ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔር ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን ትድናለህና ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮ ይድናልና" ተብሎ የተነገረውን ከሚከተሉት ጥቅሶች ጋር ያነጻጽሩ ሮሜ 10÷9-10, ኢሳ 40÷3 እና ማር 1÷1-3

### 4.2 *አባቴ በማለት እግዚአብሔርን በመጥራት ዕሩየ መለኮትነቱን ገለጸ፤*

"ኢየሱስ ግን አባቴ እስከዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ ብሎ መለሰላቸው እንግዲህ ሰንበትን ስለሻረ ብቻ አይደለም ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ እግዚአብሔር አባቴ ነው ስላለ ስለዚህ አይሁድ ሊገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር።" (ዮሐ 5÷17-18)

"አይሁድም ስለመልካም ሥራ አንወግርህም ስለስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት" (ዮሐ 10፥33) ለሞት ያበቃውም አምላክነቱን መግለጹ ነበር። (ማቴ 26፥64-66)

### 4.3 *ቅዱሳን አዕማደ ቤ/ክ ሐዋርያትም እግዚአብሔር ነው ብለው አስተምረዋል፤*

"በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ . . . ቃልም ሥጋ ሆነ።" (ዮሐ 1፥1,14)

"በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤ/ክ ትጠብቋት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ" (ሐዋ 20፥28) ተብሎ የተጻፈውን ማስተዋል በቂ ነው።

### 4.4 *የቃሉ አገልጋዮች ሐዋርያት አምላክ በማለት አስተምረዋል፤*

"ቶማስም ጌታዬ አምላኬም በማለት መለሰለት" (ዮሐ 20፥28) አንዳንድ መናፍቃን ሙሴም አምላክ ተብሏል (ዘጸ 7፥1) ሰዎችም አማልክት ተብለዋል (መዝ 81፥6) ኢየሱስም አምላክ መባሉ እግዚአብሔርነቱን አይጠቁምም ይላሉ ነገር ግን ይህን ቃል ባለቤቱ የተረጎመው በመሆኑ እንመልከተው።

"ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው፡- እኔ አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን? መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን ትሳደባለህ ትሉታላችሁን? እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑኝ ባደርገው ግን እኔን ስንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንደሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ።" (ዮሐ 19፥34-38) በማለት መለኮታዊ ሥራው መለኮታዊነቱን እንደሚገልጽና መለኮታዊ እንደሆነም እንድናምን ገልጾልናል። ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችም ይህን መለኮታዊ ቃል ያዳብሩታል "እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ ነው አሜን" (ሮሜ 9፥5) እነዚያ የእግዚአብሔር ቃል ስለመጣላቸው አማልክት ዘበጸጋ ተባሉ። እርሱ ግን ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዕሩየ መለኮት እንደመሆኑ አምላካዊ ሥራ ሠርቶ መለኮታዊነቱን ገልጾልናልና ከእነርሱ ይለያል "እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘለዓለም ሕይወት ነው፤ ልጆች ሆይ ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ።" ተብሎ እንደተጻፈ (1ዮሐ5፥21) አዎን ቅዱሳን ሐዋርያት እንዳስተማሩት ኢየሱስ በእርግጥ እውነተኛ አምላክ፣ የተባረከ አምላክ፣ የባሕርይ አምላክ ነው እንጂ አማልክት ዘበጸጋ ከተባሉት ጋር አይጐዳኝም።

### 4.5 *መጀመሪያ መጨረሻ የሌለው አልፋና ኦሜጋ ነው፤*

እኛ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ማነው? ለሚሉን ሁሉ የምንመልሰው ኦርቶዶክሳዊ መልስ እግዚአብሔር አብ መጀመሪያ መጨረሻ የሌለው ዘለዓለማዊ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ "ከመዝይቤ እግዚአብሔር አነ ቀዳማዊ ወአነ ደኃራዊ አልቦ ባዕድ አምላክ ዘእንበሌየ - እኔ መጀመሪያ ነኝ እኔም መጨረሻ ነኝ ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የለም" (ኢሳ 43፥10-13, ኢሳ 49፥6) እንዳለ።

አብ የተባለበት ጊዜ በዚህ ቀን ዓመት ወራት ጀምሮ አብ ተባለ እንደማይባል ከቅድምና አብ እንደተባለ አብም ያልተባለበት ጊዜ እንደሌለ ግልጽ ነው። "እግዚአብሔር የዘለዓለም አምላክ የምድር ዳርቻ ... አይታክትም ማስተዋሉም አይመረመርም።"


www.ethiopianorthodox.org

"ተራሮች ሳይወለዱ ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ አንተ ነህ" (መዝ 89፥2, ዘዳግ 32፥40) ተብሎ ተጽፏልና፤ ወልድም ወልድ የተባለበት ጊዜ እንዲሁ ነው አይታወቅም ወልድ ያልተባለበት ወቅት ስለሌለ።

አዎ አንድ ልጅም እንደመሆኑ ቀዳማዊና ደኅራዊ ነው። "ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘለዓ ለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ሕያው ነኝ። የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።" (ራዕ 1፥18) "አልፋና ኦሜጋ ፊተኛውና ኋለኛው መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ" (ራዕ 22፥13) አለኝ በማለት ቅዱስ ዮሐንስ መስክሯል። በተጨማሪም "በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ" (ዮሐ 1፥1-3, 1ዮሐ 1፥1) "አባቶች ሆይ ከመጀመሪያ የነበረውን አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ ጎበዞች ሆይ ክፉውን አሸንፋችሁታልና እጽፍላችኋለሁ ልጆች ሆይ አብን አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ" (1ዮሐ 2፥13) በማለት አስተምሮናል። ነቢዩ ሚክያስም "አንቺም ቤተልሔም ኤፍራታ ሆይ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፥ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘለዓለም የሆነ በእስራኤል ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል" (ሚክ 5፥2) ቅ/ጳውሎስም "እርሱም ከሁሉም በላይ ሆኖ ለዘለዓለም የተባረከ አምላክ ነው። አሜን" (ሮሜ 9፥5) ብሏል።

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ኢየሱስ ክርስቶስ በፍጥረት የማይደገፍ ለመኖሩ ፍጥረታት ምክንያት ያልሆኑት ቀዳማዊ ደኃራዊ ነው። ያልነበረበት ጊዜ የለም በጊዜ ውስጥ አልተገኘም ጊዜም አላስገኘውም በባሕርዩ "ህልው" ያለ የነበረ ጊዜ ያልተቀደመው ጊዜን ያስገኘ በባህርየ መለኮቱ ሞት በመንግሥቱ ሽረት የሌለበት የባሕርይ አምላክ ነው።



## 5 ነቢይ ነው፤

ነቢይ ማለት ያለፈውን በመንፈስ ቅዱስ የሚያውቅ ያለበት ምን እንደሚመስል የተረዳ የወደፊቱም ነገር የሚገለጥለት ማለት ነው። እግዚአ ነቢያት ክርስቶስም ፈጻሜ ትንቢተ ነቢያት ሆኖ በመምጣቱና የነቢይነት ሥራ በመሥራቱ ነቢይ ተብሏል። ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢይ እንደሆነ በቃሉ ሲናገር "ዳሩ ግን ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይጠፋ ዘንድ አይገባምና ዛሬና ነገ ከነገ በስቲያም ልሄድ ያስፈልገኛል።" አለ (ሉቃ 13፥33) "ኢየሱስ ግን ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ቤቱ በቀር ሳይከበር አይቀርም" (ማቴ 13፥57) አለ። በትንቢትም ሙሴ ነቢይ ብሎ ጠርቶታል "እግዚአብሔርም አለኝ የተናገሩት መልካም ነው ከወንድሞቻቸው መካከል እንደአንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ።" (ዘዳ 18፥17-18) የዚህ ትንቢት ፍጻሜ በሐዋ 7፥37-40 በቀዳሜ ሰማዕት በእስጢፋኖስ ስብከት ተገልጿል።

መሐመዳውያን በድፍረት ይህን የተገለጠውን ወንጌላዊ ቃል በመለወጥ ወይንም ተጽፎ በባለቤቱ የተተረጎመውን መለኮታዊ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ እንኳን መወሳት ያልታሰበውን ራሱን በነቢይ ስም የጠራውን ሐሣዊ ለመተርጎም ስለእርሱም እንደተነገረ ለማስመሰል ጥረዋል። ሆኖም እግዚአብሔር የፈጠራት ጆሮ ውሸታቸውን ለመቀበል ባለመፈለጓ ሰሚ አላገኙም። "ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢይ ወሐዋርያ" እንዳለ ደራሲ (መልክአ ኢየሱስ)

ኦርቶዶክሳዊ ሆይ ኢየሱስ ነቢይ በመሰኘቱ እንደነኤልያስ፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ . . . ፍጡር የተባለ (የሆነ) አይምሰልህ። የነቢያትን ትንቢት "እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም" ብሎ እንደተናገረ የፈጸመ፤ ነቢያት ለፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን እንደመሰከሩ እርሱም

www.ethiopianorthodox.org

ለኃጢአታችን የምናመካኘው እስክናጣ ድረስ "እኔ መጥቼ ባልነገርኋቸውስ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር። አሁን ግን ለኃጢአታቸው ምክንያት የላቸውም" (ዮሐ 15÷22) ብሎ እንደተናገረው ስላስተማረ በነቢያት አድሮ እቅዱን ለሰው ልጆች ይገልጽ የነበረ አምላክ በዘመኑ መጨረሻ በልጁ በእርሱ በኩል ስለተናገረን የብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት አገልግሎት በእርሱ ሊቀካህናትነት እንደተፈጸመ የነቢያትንም ትምህርት እግዚአብሔር "ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ።" (ዕብ 1÷1-3) ተብሎ እንደተጻፈ ይፈጸም ዘንድ እኛን ስላለፈው፣ ስለሚመጣው ስላለው ሁሉ ስላስተማረን ነቢይ አልነው ወይም ተባለ እንጂ ለነቢያት ትንቢትን የገለጸ ሁሉን የሚያውቅ አምላከ ነቢያት እግዚአ-ነቢያት መሆኑ ተዘንግቶ አይደለም።

## 6. *በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ ሰውና እግዚአብሔርን (እግዚአብሔርነቱን) ያስታረቀ ሊቀ ካህናት ነው።*

በብሉይ ኪዳን በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆነው የሚያስታርቁ ሊቃነካህናት ነበሩ። ሊቃነ ካህናቱም በሚሾሙበት ጊዜ መንፈሰ-ረድኤት እንዲያድርባቸው በዘይት ይቀቡ ነበር። (ዘጸ 29÷1-9) ቤተመቅደስንም ያስተዳድሩ ካህናትንም ይቆጣጠሩ ነበር (1ሳሙ 3÷12-13, 2ነገ 12÷7, 22÷4) የአይሁድንም ሸንጎ በሊቀመንበርነት ይመሩ ነበር (ማቴ 26፤57-65) በማስተስረያ በዓልም የሕዝቡን ኃጢአት ለማስተሥረይ በዓመት አንድ ጊዜ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብተው ታቦቱ ላይ ደም ይረጩ



www.ethiopianorthodox.org

እንደነበር በዘሌ 16 ላይ ተጽፎ ይገኛል። ሊቃነ - ካህናቱ ይሰዉት የነበረው ደመ በግዕ፣ ሥጋ በግዕ፣ ደመ ጠሊ፣ ሥጋ ጠሊ፣ ደመ ላህም፣ ሥጋ ላህም ይመጣ ዘንድ ያለው የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው አማናዊ መሥዋዕት የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ምሳሌ እንደነበር ሁሉ ሊቀ ካህናቱም የኢየሱስ ክርስቶስ ምሣሌ ነበር። አሁን በምድራዊ አገልግሎት የሰው ዘር የሚያዘግምበት ወቅት ተፈጽሟል፤ ሰማያዊው ሊቀ ካህናት አንድ ጊዜ በሠዋው መሥዋዕት አንድ ጊዜ በጸለየው ጸሎት የሚያጸድቅበት ጊዜ ሆኗል። (ዕብ 9÷1-22, ዕብ 10÷12-21)

በአንደኛ ጢሞቴዎስ "አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛ (ምርጥ) ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ ይህም በገዛ ዘመኑ ምሥክርነቱ ነበረ።" (1ጢሞ 2÷5-6) ተብሎ የተጻፈውን በመጥቀስ አስታራቂነቱን የሚመለከት ቃል መሆኑን ዘንግተው መናፍቃን "በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የሆነ ደግሞ አንድ አለ" የሚለውን በመጥቀስ አምላካዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርየ መለኮቱ ከአብ ዝቅ ከሰው ብቅ ያለ አድርገው ይገምቱታል። ነገር ግን ከላይ የተጠቀሰው ክፍል የሚያመለክተው በኃጢአቱ ከእግዚአብሔር የራቀውን ሰውና በሰው በደል መለኮታዊ ቁጣው ከሰው ያራቀውን አባቱን፣ መንፈስ ቅዱስን (መለኮታዊነቱን) በዮሐንስ "እምከመ ተለዐልኩ እምድር እስሕብ ኵሎ ኀቤየ እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልኩ እንደሆን (ከፍ ብዬ እንደተሰቀልኩ) ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ።" (ዮሐ 12፤32) ብሎ እንደተናገረ ከሰማይ ዝቅ ከምድር ከፍ ብሎ ተሰቅሎ ሰውና እግዚአብሔርን ማገናኘቱን ነው የሚገልጸው እንጂ መዓርገ መለኮትን የሚያበላልጥ ጥቅስ አይደለም።

ይህም የኢየሱስ ክርስቶስ የማስታረቁ ትምህርት በቤተክርስቲያን የተለመደ መሆኑን በሚከተሉት ጥቅሶች ልብ ማለት ይቻላል።

"ወኮነ ዐራቄ ለሐዲስ ኪዳን" ለአዲስ ኪዳንም አስታራቂ ሆነ (ቅዱስ ኤፍሬም በእሑድ ውዳሴ ማርያም) "ወአቅረበነ ኀበ እግዚአብሔር አቡሁ - ወደ አባቱ ወደ እግዚአብሔር አቀረበን" (ዝኒ ከማሁ) የቅዳሜ ውዳሴ ማርያም "ፍቅረ ለነ ኀበ አቡከ ገበርከ ወአረቀ ማዕከሌነ - በእኛና በአባትህ መካከል ፍቅርን አደረግህ በመካከልም ሆነህ አስታረቅሽን" (ኪዳን)።

"ፍኖት ለኀበ አቡሁ አንቀጽ ዘመንገለ ወላዲሁ - ወደ አባቱ ለመሄድ መንገድ ለመግባትም በር" "ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ - ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" (አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሰዐታት) "ወአረቀ ትዝምደ ሰብእ ምስለ እግዚአብሔር ሊቀካህናቲሁ ለአብ - የአብ ሊቀ ካህናት የሰውን ወገን ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ" (አመክንዮ ዘሐዋርያት)

- "... እስመ ውእቱ ይተነብል በእንቲአነ ለእለ አጥረየነ ሎቱ ሕዝበ ጻድቀ ቀናዔ ለምግባረ ሠናይ"

  "... በጐ ሥራ ለመሥራት የምንቀና ደግ ወገን አድርጐ ገንዘብ አደረገን ለእኛ ማልዷልና የምናምንበት ሊቀ ካህናት (አስታራቂ) አለው።"

  (ዮሐንስ አፈወርቅ ም. 63 ቁ.26)
- "ወመጽአ ክርስቶስ አራቂ ማዕከለ እግዚአብሔር ወእጓለ እመሕያው ወዐረቆሙ ለክልኤሆሙ"

  "እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስማማ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሁለቱንም አስታረቃቸው።"

  (ዮሐንስ አፈወርቅ ምዕ 68፥21)



www.ethiopianorthodox.org

"ወሰአሎ ለአብ ያኀልፍ እምኔነ መዓተ ዘረከበነ እምቅድም ከመ ዘለሊሁ ይጌልቍ ስእለተ ሎቱ እስመ ውእቱ ነሥአ አምሣሊነ ከመ ይስአሎ ለአብ በእንቲአነ ከመ ምዕረ ዳግመ ይዝክረነ ወኢይኅድገነ እምኔሁ ወኮነነ ጥንተ ወበኵረ ለኵሉ ምግባረ ሠናይ እግዚእነ ክርስቶስ ወጥንተ ሕይወት አስተዳለወ ለነ ከመ ዘይትሜነይ ይርከብ ግብረ እምኀበ አብ በትስብዕቱ ወቅድመ አስተዓለወ ዘንተ ለህላዌ ዚአነ ውእቱሰ ፍጹም ውእቱ በርእሱ ወኢየኀጽጽ ምንትኒ ግሙራ በመለኮት ወሥጋሂ እንከ ዘነሥአ ዘበአማን ኮነ ሎቱ ለባሕቲቱ"

"እርሱ ራሱ ልመናን የሚሻ መስሎ በጥንት ጀምሮ ያገኘን ፍዳ ከእኛ ያርቅ ዘንድ አብን ማለደው እንደገና ደግሞ እንዲያስበን ከእሱም እንዳይለየን ስለኛ አብን ይማልደው ዘንድ ባሕርያችንን ነሥቷልና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለበጐ ሥራ ሁሉ ጀማሪ አብነት ሆነን ሰው በመሆኑ ከአብ ርዳታን ያገኝ ዘንድ የሚሻ መስሎ ለእኛ ትንሣኤን አዘጋጀልን ለእኛ ባሕርይ አስቀድሞ ልጅነትን አዘጋጀ እርሱ ግን በባሕርይ ፍጹም ነው በባሕርዩ ፈጽሞ ምንም ሕፀፅ የለበትም የተዋሐደውን ሥጋ ከተዋሐደ በኋላ ለእርሱ ብቻ በእውነት ገንዘቡ ሆነ"

(ቄርሎስ ምዕ 79፥38)

"ወአስተርአየ ይእዜ ቅድመ እግዚአብሔር በእንቲአነ ወበዐይ ገጽ ኢኮነ ክሡተ ቅድመ እግዚአብሔር እምቅድመ ይሠጉ አላ ውእቱሰ ክሡተ ኀቤሁ ወገባሬ ኵሉ ውእቱ በዕረፍት ዘእንበለ ጻማ ወውእቱ ጥበቡ ለአብ ዘቦቱ ኵሉ ኮነ

"ዛሬም ስለእኛ በእግዚአብሔር ፊት ተገለጠ ሰው ከመሆኑ በፊት በእግዚአብሔር ፊት ለምን አልተገለጠም? እርሱማ በህልውና ያለ ያለ ድካም ሁሉን የፈጠረ ሁሉ የተፈጠረበት የአብ ጥበቡ ነው እንጂ"

(ቄርሎስ 79፥71)

- “ወበዐይ አምሳል አስተርአየ ይእዜ ቅድመ እግዚአብሔር አስተርአየ በግብር ሐዲስ ቃል ቅዱስ ለቢሶ ሥጋ ከማነ እንዘ ውእቱ ህልው በመለኮቱ ኀበ አብ እምቅድመ ዓለም ወእምቅድመ ይሠጉ ወአስተርአየ ይእዜ ቅድመ እግዚአብሔር በእንቲአነ በህላዌነ”

“ዛሬስ በምን ሥራ በምን ነገር በእግዚአብሔር ፊት ተገለጠ አምላክ ቃል እንደ እኛ ሰው ሆነ በአዲሱ ሥራ ተገለጠ ዓለም ሳይፈጠር ሥጋንም ሳይዋሐድ በመለኮቱ በአብ ዘንድ ህልው ሲሆን ዛሬ ስለእኛ በእግዚአብሔር ፊት በኛ ባሕርይ ተገለጠ”

(ቄርሎስ ምዕ. 79፥72)

- “ወእምድኅረ ኮነ ሰብአ ተሰምየ ብእሴ ወመሢሐ ወኢየሱስሃ ወታቦተ ወዐራቄ ወበኲረ ለዘይትኑ-ሣእ እሙታን ወርእሰ ሥጋሃ ለቤተ ክርስቲያን ወካልአን አስማት ዘከመገዘ ይተልዉ ዘብሉይ ወዘሐዲስ ወዘደኃሪ መዋዕል ኵሎሙ ዘዚአሁ እሙንቱ ወውእቱ አሐዱ ከመ ወውእቱ አምላክ ጽድቅ እምቅድመ ትስብዕቱ ወአዲመ ውእቱ ህልው በግብሩ በከመኮነ ቦቱ እንዘ ህልው ቦቱ ዘልፈ ለዓለመ ዓለም”

“ሰው ከሆነ በኋላም ብእሲ፣ መሢሕ፣ ኢየሱስ፣ ታቦት፣ አስታራቂ፣ ለሙታን በኩር፣ ከሙታን ወገን ለሚነሣም በኩር፣ የምዕመናን ገዥ፣ ፈጣሪ ተባለ እንዲህ ያሉ ሌሎች ስሞችም ይነገሩለታል በብሉይ በሐዲስ ሰው ከመሆኑ በፊትና ሰው ከመሆኑም በኋላ የተነገሩ ስሞች ሁሉ የእርሱ ገንዘቦች ናቸው። እርሱ መቼም መች አንድ ነው፣ ሰው ከመሆኑ አስቀድሞ የባሕርይ አምላክ ነው፣ ወዲህም ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር እንደመሆኑ በነበረበት ባሕርይ በጌትነቱ ጸንቶ ይኖራል”

(ቄርሎስ ምዕ 81፥8)።



www.ethiopianorthodox.org

- ወአኮ ይኩነነ እኅወ ባሕቲቶ አላ ተሣሃለነ ፈድፋደ ወፈቀደ ዓዲ ይኩነነ ሊቀ ካህናት ለኀበ አብ ከመ ይስረይ ኃጢአተነ ወበእንተ ዝንቱ ወሰከ በዲበ ነገሩ ወይቤ ከመ ይኩኖሙ መሐሬ በኵሉ ምዕመን ሊቀ ካህናት ለመንገለ እግዚአብሔር ከመ ይስረይ ኃጢአተ ሕዝብ

“ሰው የሆነም ዘመድ ሊሆነን ብቻ አይደለም፤ ፈጽሞ ይቅር አለን፣ ኃጢአታችንን ለማስተስረይ ከአብ ጋር ለማስታረቅ ሊቀ ካህናትም ይሆነን ዘንድ ወደደ እንጂ። ስለዚህም ሰዎችን ሊመስላቸው ይገባል ባለው ነገሩ ላይ ጨምሮ በሁሉ አዛኝ የሕዝቡንም ኃጢአት ለማስተስረይ በእግዚአብሔር ዘንድ የታመነ አስታራቂ ይሆናቸው ዘንድ ነው።”

(ዮሐ አፈወርቅ ምዕ. 62፥13)

- “ወኢይት ከሐል ያቅርቡ ምንተኒ ዘእንበለ በአራቅይናሁ ለክርስቶስ”
“በክርስቶስ በተገኘው እርቅ በኩል ካልሆነ በቀር በሌላ በምንም በኩል ማቅረብ አይቻልም”

(ዮሐ. አፈወርቅ)

- “ሰአል እምኔየ እሁበከ አሕዛበ ለርስትከ”
“ከእኔ ለምን አሕዛብንም ለርስትህ እሰጥሃለሁ”

(መዝ. 2፥8)

የቁስጥንጥንያ ሊቀ ጳጳስ ኤራቅሊስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው መሆኑን ሲያስተምረን “የሰው ሁሉ ነጻነት የተጻፈበት ቅዱስ ማኅፀን እንደምን ያለ ነው? በእኛ ሰልጥኖ የነበረ ሞትን የሚቃወመው የጦር ዕቃችን (ክርስቶስ) ያደረበት ቡሩክ ማኅፀን እንደምን ያለ ነው? እንደ ዕፀ ሠሉስ ያለ ዘር በባሕርይ ሁሉን በሚያስገኝ በመንፈስ ቅዱስ ጌታን ያስገኘችልን የተመረጠች ገራህት (ማርያም) እንደምን ያለች ናት፣

እግዚአብሔር እንደቸርነቱና እንደ ይቅርታው እንደ መልከ ጼዴቅ ባለ ሹመት ለማገልገል ሥጋን ለብሶ ባሕርዩ ሳይለወጥ ታላቅ ካህን የሆነበት መቅደስ እንደምን ያለ ነው" ብሎ እንደተናገረ።

(ሃ. አበው ዘአክርስቶዶሎስ ምዕ. 112÷23-24

ከዚህ በላይ ያየናቸው ሊቃውንት እንደተናገሩት "ካሳ የተፈጸመበትን" አስታራቂነቱን ልብ እንበል ከዚህ በማስከተል ኢየሱስ ክርስቶስ ከብሉይ ኪዳን ሊቃነ ካህናት የሚለይባቸውን ነጥቦች እንመልከት።

## 6.1 *በሰማያት ያለፈ (ውሳጤ መንጦላዕት የገባ) ሊቀ ካህናት ነው።*

"እንግዲህ በሰማይ ያለፈ (ውሳጤ መንጦላዕት የገባ) ትልቅ ሊቀካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።" (ዕብ 4፥14) እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ የብሉይ ኪዳን ሊቃነ ካህናት ግን የሚገቡት ወደምድራዊ ድንኳን ነበር።

## 6.2 *በድካማችን የሚራራ ሊቀካህናት ነው።*

"ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ *በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀካህናት የለንም*" (ዕብ 4÷15) የብሉይ ኪዳን ሊቀካህናት ለሰዎች የሚራራ ራሱ ደግሞ ኃጢአት ስለሚሠራ ነው የሚራራው። የሰውን ድካም በራሱ ድካም ስለሚረዳው ነው (ዕብ 5÷2-3) ኢየሱስ ግን እንደኛ ደክሞ ኃጢአት የማይሠራ ጻድቀ-ባሕርይ ሲሆን ይራራልናልና። ርኅራኄው ልዩ ነው (ዕብ 4÷15, 2÷22, ዮሐ 8÷45-46)



## 6.3 *የማይለወጥ ክህነት ያለው ካህን ነው።*

"እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው *እርሱ ግን ለዘለዓለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው።"* እንዳለ የእግዚአብሔር ሰው (ዕብ 7÷23-24)። የብሉይ ኪዳን ሊቃነካህናት በሞት ስለሚለወጡ አንዱ ሞቶ አንዱ ይሾም ስለነበር የሊቀ ካህናቱ ሹመት ቀዋሚ አልነበረም። ስለዚህ ካህናት የሆኑ ብዙዎች ነበሩ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሞትን ድል ነስቶ በሕይወት ስለሚኖር ክህነቱም (ኃጢአትን የማስተሠረይ ችሎታው) የባሕርዩ ሲሆን የባህርዩ የሆነውን ለእነርሱ በጸጋ ሰጥቷቸው ነበርና ሥጋ ለብሶ በክህነት ሲገለጥ ባሕርያዊ ሥልጣኑ የማይሻር ሆነ ማለት ነው።

## 6.4 *ሞትን አሸንፎ በሕይወት የሚኖር ሊቀ ካህናት ነው።*

"የማይለወጥ ክህነት አለው ስለእነርሱም ሊያማልድ *ዘወትር በሕይወት ይኖራልና* ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።" እንዳለ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ (ዕብ 7÷25) ይህ ጥቅስ በአበው ትርጓሜ በሱ አስታራቂነት ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ማዳን ይቻለዋል። ተብሎ ተብራርቶ ተተርጉሟል (አንድምታ ትርጓሜ ጳውሎስ ይመልከቱ)

## 6.5 *በእርሱ በኩል (እርሱን አምነው) ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ሊያድን የሚችል ሊቀካህናት ነው።*

"የማይለወጥ ክህነት አለው ስለእነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና *ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።"* (ዕብ7÷25, ገዘኒከማሁ) በክርስቶስ አምነው ምዕመናን እንደሚድኑ መድኀኒታችን እንዲህ አለ። [illegible] እላችኋለሁ እኔ የበጎች በር ነኝ።" (ዮሐ 10÷7)

www.ethiopianorthodox.org

“በሩ እኔ ነኝ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል።” (ዮሐ 10÷9)

“እኔ መንገድና እውነት ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።” (ዮሐ 4÷6-7) ተብሎ እንደተጻፈው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ማለት ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ የሚኖር ሰው ሕይወትን ያገኛል ከእግዚአብሔር ቃል እንደሰማነው የሕይወት መሥመር ክርስቶስ ነውና። ማንም ይሁን ማን ክርስቶስን ካላመነ ቢጾምም ቢጸልይም ያለክርስቶስ ዋጋ የለውም በክርስቶስ እንጂ ዓለም በራሱ ሕይወት የለውምና በክርስቶስ ቤዛነት የማያምን በሌላ በምንም መንገድ አይድንም።

*አንባቢ ሆይ! ልብ ይበሉ* - አሁን ባነበብነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ዕብ 7÷25 ማለት ነው ስለእነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል የሚለውን ቃል ሲያነቡ ኢየሱስ ዛሬ ሁሉ ወደፊትም ሲወድቅ ሲነሣ ሲያማልድ ይኖራልን ብለው ጠይቀው ያውቃሉን? መቼም አማልዶአል አማልዶ ነበር ስላላለ ያማልዳል ስላለ ነገሩ ከአሁን ቀደም ያልተፈጸመ መስሎዎት ይሆናል ነገር ግን ከአሁን ቀደም ሥጋ በመሆኑ ወራት በጸሎት በምልጃ ወደ እግዚአብሔር ስላቀረበዎት ለመዳንዎትም ቤዛና መድኃኒት ስለሆነዎ ተስፋው ተፈጽሟልና ከአሁኑ በኋላ የሚወድቅ የሚነሳ እንዳይመስልዎ (ዕብ 5÷7-10) እና ለምን ያማልዳል አለ ብለው ከጠየቁ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ የዕለተ ዓርብ የማስታረቅ አገልግሎቱን ከአዳም መፈጠር ጀምሮ እስከዕለተ ዓርብ ላሉት ሁሉ እንደሆነ፤ ተሰቅሎ ሞቶ ራሱን ሰውቶ እንዳስታረቀ ለመግለጽ ሲፈልግ መጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቱን በኋላፊ እንደሚከተለው ገልጾት ይገኛል።

“ብዙ ውሾች ከብበውኛልና የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ አጥንቶቼ ሁሉ ተቆጠሩ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ።” (መዝ 21፤16-18)



“የተናቀ ከሰውም የተጠላ፣ የሕማም ሰው ደዌንም የሚያውቅ ነው፤ ሰውም ፊቱን እንደሚሰውርበት የተናቀ ነው እኛም አላከበርነውም። በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል እኛ ግን እንደተመታ በእግዚአብሔርም እንደተቀሠፈ እንደተቸገረም ቆጠርነው እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ስለበደላችንም ደቀቀ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።” (ኢሳ 53፤3-5)

“ተጨነቀ ተሠቃየም አፉንም አልከፈተም ለመታረድ እንደሚነዳ ጠቦት በሸላቾቹም ፊት ዝም እንደሚል በግ እንዲሁ አፉን አልከፈተም በማስጨነቅ በፍርድ ተወሰደ፤ ስለ ሕዝቤ ኃጢአት ተመትቶ ከሕያዋን ምድር እንደተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ? ከክፉዎችም ጋር መቃብሩን አደረጉ ከባለጠጎችም ጋር በሞቱ ሆኖም ግፍን አላደረገም ነበር። በአፉም ተንኰል አልተገኘበትም ነበር እግዚአብሔር በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቅዶ ነፍሱን ስለ ኃጢአት መስዋዕት ካደረገ በኋላ ዘሩን ያያል ዕድሜውም ይረዝማል፤ የእግዚአብሔርም ፈቃድ በእጁ ይከናወናል።” (ኢሳ 53፤7-10)

“ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሣል ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና ከዓመፀኞችም ጋር ተቆጥሮአልና እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢአት ተሸከመ፣ ስለዓመፀኞችም ማለደ” (ኢሳ 53÷12)

“እግዚአብሔርም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፤ የወይን ስካር እንደተወው እንደ ኃያልም ሰው።” (መዝ 77÷65)

“አምላክ በእልልታ እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ” (መዝ 46÷5) ከዚህ በላይ በተመለከትነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እጄን እግሬን ይቸነክሩኛል በማለት ፈንታ ቸነከሩኝ . . . ወዘተ ብሎ ዳዊት መናገሩ

www.ethiopianorthodox.org

ኢሳይያስም ስለአመፀኞች ይማልዳል ስለበደላችንም ይደቅቃል በማለት ፈንታ ደቀቀ ማለቱ በድጋሚ ዳዊትም ከሙታን ተለይቶ ይነሣል በማለት ፈንታ ተነሳ ያርጋል በማለት ፈንታ ዐረገ ብሎ መናገሩ ኢየሱስ የማዳን ሥራውን ፈጽሞ እንዳይደለ (ቅድመ ሥጋዌ እንደሆነ) ግልጽ ነው። ነገር ግን የዕለተ ዓርብ ማዳኑ ለእነርሱም መጽደቂያቸው ስለሆነ ስለከበሩበትም እንደተፈጸመላቸው አድርገው በተስፋ ተናግረውታል።

በአዲስ ኪዳን ደግሞ ተፈጽሞ ሳለ የማዳን ሥራው የድካም አገልግሎቱ እንዳልተፈጸመ አድርጎ ይማልድልናል ማለቱ እስከ ዕለተ ምጽዓት የሚፈጠረው ፍጥረት በዕለተ ዓርብ የማስታረቅ አገልግሎቱ እያመነ እንደሚድን ይገልጻል እንጂ እንደ ብሉይ ኪዳን ሊቃነ ካህናት የሠዋው መሥዋዕት ተረፈ ኃጢአት አስቀርቶበት ያን ለማስተካከል የሚወድቅ የሚነሣ ሆኖ አይደለም። የሊቀ ካህናቱ ጸሎት መሥዋዕት ምልአተ ኃጢአትን ለመደምሰስ አንድ ጊዜ ተፈጽሟል። ይልቁን "ይማልድልናል" የሚለው ቃል ዛሬም የዕለተ ዓርቡ ቤዛነት ካሳ ሞት ደም መፍሰስ አዲስ በየዕለቱ ንስሐ የሚገቡበትን የሚያቀርብ የሚያድን መሆኑን ያስተምረናል።

## 6.6 <u>ስለ ራሱ መሥዋዕት የማያሻው ነውር የለሽ ሊቀ ካህናት ነው።</u>

በብሉይ ኪዳን ይሾሙ የነበሩ ሊቃነ ካህናት እነርሱም እንደ ማንኛውም ሰው ኃጢአተኞች ስለነበሩ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር በመሥዋዕት፣ በጸሎት ከማስታረቃቸው በፊት ስለራሳቸው የኃጢአት ሥርየት አስቀድመው መዋዕት ይሰው ነበር። በዘሌዋውያንም "ሙሴም አሮንን ወደመሠዊያው ቀርበህ የኃጢአትህን መሥዋዕትና የሚቃጠለውን መሥዋዕትህን ሠዋ ለራስህ ለሕዝቡም አስተሥርይ እግዚአብሔርም



www.ethiopianorthodox.org

እንዳዘዘ የሕዝቡን ቁርባን አቅርብ አስተሥርይላቸውም አለው።" (ዘሌ <u>9፥7</u>) ተብሎ እንደተጻፈው ይህንን ቃል በመጥቀስ የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊም "በዚህ ምክንያት ስለሕዝብ እንደሚያቀርብ እንዲሁ ስለራሱ ደግሞ መሥዋዕት ስለኃጢአት ሊያቀርብ ይገባዋል እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም" (ዕብ <u>5፥3-4</u>) በማለት አብራርቷል።

ስለ ኢየሱስ ሊቀካህናትነት ግን <u>*"እርሱም እንደነዚያ ሊቃነ ካህናት አስቀድሞ ስለራሱ ኃጢአት በኋላም ስለሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጎአልና።"*</u> (ዕብ <u>7፥27</u>) በማለት ከብሉይ ኪዳን ሊቃነ ካህናት ይለየዋል። ለምን ኢየሱስ ስራለሱ መሥዋዕት አላስፈለገውም የሚል ሰው ቢኖር ጻድቀ ባህርይ፣ ንጹሐ ባሕርይ፣ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለበት በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን የሚያድል መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን የሚያርቅ ቡሩክ አምላክ ስለሆነ ነው ብለን እንመልስለታለን። ኢየሱስ ክርስቶስ የዚህ ዓለም ገዥ ዲያብሎስ ነውር ያላገኘበት (ዮሐ <u>14፥30</u>) በአንደበቱ ሐሰት ያልተገኘበት (1ጴጥ <u>2፥22</u>) ማንም ስለኃጢአት ይህን አደረገ ብሎ የማይወቅሰው (ዮሐ <u>8፥46</u>) ንጹሕ ቅዱስ ስለሆነ መሥዋዕት አያሻውም።

## 6.7 <u>በመሐላ የተሾመ ሊቀካህናት።</u>

መሐላ የማይለወጥ ነገርን ያመለክታል አንድ ሰው ይህን አላደርግም እንዲህም አላደርግም ብሎ ከማለ የነገሩን ሐቅነት ያመለክታል። "ሰዎች ከእነርሱ በሚበልጠው ይምላሉና ለማስረዳትም የሆነ መሐላ የሙግት ሁሉ ፍጻሜ ይሆናል፤ ስለዚህም እግዚአብሔር የተስፋውን ቃል ለሚወርሱ ፈቃዱ እንደማይለወጥ አብዝቶ ሊያሳያቸው ስለፈቀደ እግዚአብሔር ሊዋሽ በማይቻል በሁለት በማይለወጥ ነገር

በፊታችን ያለውን ተስፋ ለመያዝ ለሸሸን ለእኛ ብርቱ መጽናናት ይሆንልን ዘንድ በመሐላ በመካከል ገባ ይህም ተስፋ እንደነፍስ መልሕቅ አለን እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ ወደመጋረጃውም ውስጥ የገባ ነው።" (ዕብ 6፥16-19) መሐላ ትልቅ ነው።

እንግዲያውስ ከሌዋውያን ክህነት በሚበልጥ ክህነት እንደመልከጼዴቅ ክህነት ዘለዓለማዊ በሆነ ክህነት የተሾመ ሊቀካህናት አለን "እነርሱም ያለመሐላ ካህናት ሆነዋልና እርሱ ግን ጌታ አንተ እንደመልከጼዴቅ ሹመት ለዘለዓለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይጸጸትም ብሎ በተናገረለት ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖአልና <u>ያለመሐላ ካህን እንዳልሆነ መጠን እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል።"</u> (ዕብ 7፥20-22) ተብሎ እንደተጻፈ፣ አዎን ያለመሐላ ከተሾሙት የብሉይ ኪዳን ሊቃነካህናት ይልቅ በመሐላ የተሾመ ሊቀካህናት ወልደአብ ወልደማርያም ኢየሱስ ይበልጣል። ይህንንም የተናገረበት ምክንያት አበው እንደሚሉት በክርስትና እናምን ነበር ነገር ግን ኃጢአት የሚያስተሠርይ ሊቀ ካህናት የላቸውም ሲሉ ሰምቶ ነው።

## 6.8 <u>መሥዋዕትን አንዴ (አንድ ጊዜ) ያቀረበ ሊቀካህናት።</u>

<u>"እርሱም እንደነዚያ ሊቃነካህናት አስቀድሞ ስለራሱ ኃጢአት በኋላም ስለሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጎአልና</u> ሕጉ ድካም ያለባቸውን ሰዎች ሊቀካህናት አድርጎ ይሾማልና ከሕግ በኋላ የመጣ የመሐላው ቃል ግን ለዘለዓለም ፍጹም የሆነውን ልጅ ክርስቶስ ይሾማል።" (ዕብ 7፥27-28) ተብሎ እንደተጻፈ በብሉይ ኪዳን የነበሩ ሊቃነካህናት ዕለት ዕለት ለኃጢአት ሥርየት የሚሆን መሥዋዕት ይሰዉ ነበር፤ ምክንያቱም አንድ ቀን ይሰዉት የነበረው መሥዋዕት ፍጹም ድኅንነትን ስለማያሰጥ ነው። ኢየሱስ ግን አንድ ቀን ስለዓለም መዳን



በቀራንዮ ላይ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ባቀረበ ጊዜ የዓለምን ኃጢአት ስላስወገደ በእርሱ ያመነ ሁሉ ተረፈ ኃጢአት ስለማይኖርበት በየጊዜው ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ አይገደድም፤ ዓለም ሁሉ በእርሱ ካመነ በዕለተ ዓርቡ መሥዋዕት በኢየሱስ ክርስቶስ ይድናል። ሌላም መሥዋዕት አያስፈልገውም "የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአትን ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ስለኃጢአት መሥዋዕት አይቀርብልንምና።" (ዕብ 10፥26) ተብሎ እንደተጻፈ ሌላ መሥዋዕት የለምና አንድ ጊዜ የተሠዋው በግ የኃጢአተኛ ተለዋጭ ሆኖ ስለተሠዋ ሁለተኛ መስዋዕት አይሆንም ዕለት ዕለትም አይሰቀልም አይሠዋም አንድ ጊዜ ተሠውቷልና፤ የመሥዋዕቱ በግም አንድ ነውና።

## 6.9 <u>በአባቱ ቀኝ የተቀመጠ ሊቀ ካህናት።</u>

<u>"ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው። በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀካህናት አለን፤</u> እርሱም የመቅደስና የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ ነው። እርስዋም በሰው ሳይሆን በጌታ የተተከለች ናት።" (ዕብ 8፥1-2) ተብሎ እንደተጻፈ ራሱን የሰው ልጅ ብሎ የሚጠራው ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማይ እንደወረደ ዮሐ 3፥13 ላይ ተጠቅሶአል። ወረደ የሚለው ቃል ለምልአተ መለኮቱ ውሳኔ ለሌለው ለመለኮታዊ ቃል የሚስማማ ሆኖ አይደለም። ሰው ሆኖ፣ ሥጋ ለብሶ፣ ባጭር ቁመት፣ በጠባብ ደረት ተወስኖ፣ ለድኅነተ ዓለም፣ ለሥራ መገለጡን ሲጠቁም ለሕማም፣ ለሞት፣ ለመሥዋዕትነት መምጣቱን ለመግለጽ ነው እንጂ። እንደዚሁ ተቀመጠ የሚለው ቃል ደግሞ የሚያመለክተው ሥራውን መጨረሱን "ወነደገ ንድየተ ኅላዌ ዘቀዳሚ ገብአ ወተመይጠ ኀበ ስብሐቲሁ ወክብሩ" የቀደመ የድኅነት ኑሮውን ተወ ወደቀደመ ክብሩ ተመለሰ ተብሎ በሊቃውንቱ እንደተነገረ ወደ ቀደመ መለኮታዊ ጌትነቱ መመለሱን ይጠቁማል እንጂ ለምልዐተ [illegible] ተወስኖለት አይደለም። ሐዋርያው በዚህ መልእክቱ

www.ethiopianorthodox.org

"ኃጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ።" (ዕብ 1፥3) ብሏል። ተቀመጠ በሚለው ቃል ሌላው ልብ ልንለው የሚገባው የመዳን ምሥጢር ደግሞ ከምልአተ መለኮቱ የተወሰነበት ወቅት ኖሮ መንበረ ክብሩን ተቆጣጠረ ማለት ሳይሆን ሰው በመሆኑ ሰማያዊ ያልነበረውን የሰውን ባሕርይ ማክበሩንና በእርሱ ክብር መክበራችንን በክብር ቦታ መቀመጣችንን የሰው ልጅ ሁሉ በኢየሱስ መክበሩን ነው። (ኤፌ 2፥6-7) የሚያመለክተው።

## 6.10 *በገዛ ደሙ ወደቅድስተ ቅዱሳን የገባ ሊቀካህናት።*

"ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀካህናት ሆኖ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሠራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን የዘለዓለምን ቤዛነት አግኝቶ *አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም።"* (ዕብ 9፥11-13) አባቶቻችን ይህንን ክፍል ሲተረጉሙ ደብተራ ወይም ድንኳን የሚለው ቃል መስቀል ነው፤ ቅድሰተ-ቅዱሳን የሚለውን ደግሞ ዕገዘ አብ (በአብ ጀርባ መሰማት) ገጸ-አብ (በአብ ፊት መገኘት) ነው ብለው ተርጉመውታል። የትርጓሜያቸውን መንፈስ ለመረዳት ግን ክፍሉን በረጋ መንፈስ ማንበብን ይጠይቃል የትርጓሜው ሙሉ ቃልም የሚከተለው ነው።

"ለምትመጣው ሕግ ለወንጌል ሊቀካህናት ሆኖ የመጣው ክርስቶስ ግን በምክንያተ ዘርዕ ያይደለ እንበለ ዘርዕ - ወደተገኘች ወደ ደብተራ ርዕሱ፣ በሰው ፈቃድ ያይደለ በርሱ ፈቃድ ወደተተከለች ደብተራ መስቀል ደመ ላሕም፣ ደመ ጠሊን ይዞ የገባ አይደለም፤ ደሙን ይዞ አንድ ጊዜ ወደ እገዘ አብ፣ ወደገጸ አብ ገባ እንጂ" ብለውታል በዐይነ-መንፈስ ለተመለከተው ግሩም ነው።።



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁ አሮን ለኃጢአት መሥዋዕት ወይፈን ለሚቃጠል መሥዋዕትም አውራ በግ ይዞ ወደ ተቀደሰ ሥፍራ ይገባ ነበር (ዘሌ 16፥3) እንደተጻፈ በደመ በግዕ በደመ ላህም ወደቅድስተ ቅዱሳን አልገባም የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ (መሥዋዕት) እርሱ ራሱ ነበርና በገዛ ደሙ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገባ እንጂ (ዮሐ 1፥29)

ከዚህ ላይ ሊስተዋል የሚገባው ምሥጢር ቢኖር አይሁድ እንደወንበዴ ከወንበዴዎች ጋር የሰቀሉት የተናቀው ገሊላዊ የዓለም ሁሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ መሥዋዕት፣ ራሱ ተወካፌ መሥዋዕት (መሥዋዕት ተቀባይ) ራሱ ይቅር ባይ ራሱ ሊቀካህናት አስታራቂ መሥዋዕት አቅራቢ ሆኖ ሞተ ቀበርነው ካሉት በኋላ በሥጋው ቢሞት በመለኮት ሕያው ነውና የሕያውነት ሥራ እንደሠራ ነው። አዎን ለአይሁድ የሞተው ኢየሱስ ለእኛም ሞቶአል ነገር ግን በመስቀል ላይ እንኳ የሕያውነት ሥራ ሠርቷልና ክብር ውዳሴ ዝማሬ ለዓለም ኃጢአት ለተሠዋው በግ የዓለምን ኃጢአት በገዛ ደሙ አስተስርዮ ወደቅድስተ ቅዱሳን ለገባው ሊቀካህናት ይሁን አሜን።

## 6.11 *ደሙ ከሞተ ሥራ ሕሊናን የሚያነጻ ሊቀካህናት።*

*"የኮርማዎችና የፍየሎች ደም በረከሱትም ላይ የተረጨ የጊደር አመድ ሥጋን ለማንጻት ከሆነ ነውር የሌለው ሆኖ በዘለዓለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን?"* (ዕብ 9፥13-14) ተብሎ እንደተጻፈ በብሉይ ኪዳን ለመሥዋዕት ይቀርቡ የነበሩ የበጎች፣ የኮርማዎች፣ የጊደሮች ደም የሚያነጻው የሚቀድሰው ሥጋን ብቻ ነበር እንጂ ነፍስንና መንፈስን የሚቀድስ አልነበረም። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ሕያው መሥዋዕት ስለሆነ ሁለንተናን ሕያው ያደርጋል። የብሉይ መሥዋዕት የሚቤዠው ደመ ነፍስን ብቻ ነው ኢየሱስ ግን ሕያው መሥዋዕት ስለሆነ ሁለንተናን ሕያው ያደርጋል ኅሊናንም ከሞተ ሥራ ያነፃል።

ክርስቲያን ሆይ በእግዚአብሔር ልጅ ደም ኀሊናህን ከሞተ ሥራ ቀድሰሃልን?

## 6.12 የሐዲስ ኪዳን መካከለኛ (ምርጥ) የሆነ ሊቀካህናት።

"ስለዚህም የፊተኛው ኪዳን ሲጸና ሕግን የተላለፉትን የሚቤዥ ሞት ስለሆነ የተጠሩት የዘለዓለምን ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው።" (ዕብ 9፥15) ተብሎ ተጽፏል። መካከለኛ ተብሎ በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጎመው ቃል በግእዙ "ወበእንተዝ ለሐዲስ ሥርዓት ኢየሱስ ኅሩየ ኮነ" ለሐዲስ ኪዳን ለወንጌል መምህር ለመንግሥተ ሰማያትም አስታራቂ ሆነ ተብሎ ተተርጉሟል። "አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛ ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።" (1ጢሞ 2፥5) ተብሎ በቅ/ጳውሎስ ከተነገረው ቃለ እግዚአብሔር ጋር ተመሳሳይ ነው። የዚህንም ትርጉም ከአሁን ቀደም ስላብራራነው ልብ ብለው ይገንዘቡ አዎን ሊቃውንት እንደተረጎሙት ኢየሱስ ክርስቶስ የመንግሥተ ሰማያት አስታራቂ የወንጌል መምህር የሐዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው።

## 6.13 ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን የሻረ ሊቀ ካህናት ነው።

"እንዲህ ቢሆንስ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር፤ አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል" (ዕብ 9፥26) ተብሎ እንደተጻፈ በግ ኮርማ ጊደር ሰውቶ ሳይሆን የዓለምን ኃጢአት ያስወገደው ራሱን በመሠዋት ነው።



www.ethiopianorthodox.org

## 6.14 ያዳናቸውን ወደ መንግሥተ ሠማያት ለመውሰድ ሁለተኛ የሚገለጥ ሊቀካህናት ነው።

"ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደተመደበባቸው እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለኃጢአት ይታይላቸዋል።" (ዕብ9፥27-28) ተብሎ እንደተጻፈ ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአት በሞት ለመሻር በመጀመሪያ ጊዜ በሥጋ ማርያም እንደመጣ በሥጋ ማርያም መጥቶ ወንጌልን ሰብኮ በመስቀል ተሠውቶ ካዳናቸው በኋላ ከአሁን በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ዓለምን ለማሳለፍ ኃጥአንን ለመውቀስ ጻድቃንን ለማወደስና ሞትና ዲያብሎስን ወደጥልቁ በመጣል ለመደምሰስ መንግሥቱን ለምዕመናን ለማውረስ ይመጣል።

"የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል።" ተብሎ ተጽፏልና (የሐዋ 1፥11) በተጨማሪ ራዕይ 1፥7 ይመልከቱ።

ክርስቲያን ሆይ የኢየሱስን መምጣት ትጠባበቃለህን? አዎን ኢየሱስ ክርስቶስ ይመጣል የሚጠባበቁትን ሁሉ ከሞት ነጻ ያደርጋቸው ዘንድ ለሚጠብቁት ሁሉ ይመጣል እንግዲያውስ ከዮሐንስ ጋር እንዲህ እንበል "ይህን የሚመሰክር አዎን በቶሎ እመጣለሁ ይላል፤ አሜን ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና።" (ራዕ 22፥20) አሜን።

## ጥያቄዎች

1. ከምዕራፉ በፊት የተጠቀሰው ጥቅስ ከምን መጽሐፍ የተወሰደ ነው? ስለመጽሐፉ የሚያውቁትን ያህል ይጻፉ?
2. ኢየሱስ ማን ነው?
3. ስምንቱ ስለኢየሱስ ክርስቶስ የመሠከሩ ዋና ዋና ምሥክሮች ማን ማን ናቸው?
4. አብ የት መሠከረለት? መንፈስ ቅዱስስ?
5. በበዓለ ሃምሣ የመሠከረው ማን ነው? ዛሬስ በቤተክርስቲያን የመሠከረለት ማንነው?
6. መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ እንደመሠከረ እንዴት የት ተጽፎ ይገኛል?
7. መለኮታዊ ሥራው እንዴት ማንነቱን እንደሚገልጽ ይጥቀሱ።
8. የክርስቶስ ትምህርት ከአገልጋዮቹ አስተምህሮ በምን ይታወቃል?
9. ፊውሱስ እንዴት ነበር?
10. ሙታንን እንዴት በሥልጣኑ እንዳስነሣ በምን ይታወቃል?
11. ስለቅዱሳት መጻሕፍት ምሥክርነት ምን ተማሩ?
12. በጌታችን ትምህርት የተጠቀሱት ቅዱሳት መጻሕፍት ማን ማን ናቸው?
13. የሙሴ የሐዋርያት ምሥክርነት እንዴት ነበር?
14. ሁለቱ መጠሪያ ስሞች ማን ማን ናቸው?
15. ኢየሱስ ማለት ምን ማለት ነው?
16. ኢየሱስ የሚለውን ስም መልከጼዴቅ ከሚለው ጋር አገናዝበው የተረጎሙት ሁለቱ ሊቃውንት ማን ማን ናቸው?
17. ክርስቶስ ነው ማለት ምን ማለት ነው?
18. የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን አይሁድ ለምን ቆነጻጸሉት?
19. ቤተክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብላ በማመኗ ምን አገኘች ጸጋዎችን ይዘርዝሩ?



www.ethiopianorthodox.org

20. ኢየሱስ ማነው? የሚለው ጥያቄ ሁለተኛ መልስ ምንድነው?
21. ኢየሱስ ጌታ ነው የሚለው ስንተኛ ተራ ቁጥር ላይ ይገኛል?
22. የክብር ጌታ ማን ነው?
23. የጌቶች ጌታ ማን ነው?
24. አራተኛው መልስ ምንድን ነው?
25. ነቢይ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?
26. በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ ያስታረቀው ሊቀ ካህናት ማን ነው?
27. የብሉይ ኪዳኑን ሊቀ ካህናት ከአማናዊው ሊቀካህናት ጋር በማነጻጸር አንድነቱንና ልዩነቱን ግለጽ።
28. ስለሊቀካህናትነቱ ስንት ነጥቦችን አነበቡ?

መምህር ልዑለ ቃል አካሉ ዓለሙ
መ.ሣ.ቁ. 270
አዲስ አበባ
Leulekal Akalu Alemu
266 Robbin Street
Decatur G.A. 30030
U.S.A.